
እንደታሠረና እንደተፈታ የኖረ ነው። ያ ትልቅ በዓል፣ በነሰመነ ት/ቤት ከተከናወነ በኋላ፣ በማግሥቱ አንድ ትንግርት ተፈጠረ። ሰመነ ለአንድ ቀን ዕረፍት፣ ከሀገሩ ሞግዚታዊ ቤተሰቦቿ ጋር ለመቆየት፣ አብራቸው ከሔደች በኋላ እንደገና አልተመለሰችም። በጣም የሚደንቀው ደግሞ፣ እሷ ብቻ ሳትሆን የጠፋችው፣ ሁለቱ ቤተሰቦቿ ባልና ሚስት ጭምር ናቸው። የቀሩት የሰመነ ጓደኞች ሁሉ፣ የሷ መጥፋት ከታወቀ በኋላ፣ ብረት በያዙ ወታደሮች መጠበቅ ተጀመረ። ካሉበት ክፍልም፣ ደጋፊዎች ሳይቀሩ፣ ወደ ውጭ መውጣት ተከለከሉ።

በዓሉ በተከናወነ በአራተኛው ቀን፣ የሀገሩ መሪና እንግዳው አምባገነን ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሰው መጡ። አመጣጣቸው ሌላ በዓል ለማክበር አልነበረም። በቀረበላቸው የምርመራ ውጤት መሠረት፣ በት/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይዘሮ አማካይነት፣ ሕፃናቱን ለማነጋገርና፣ ፍርድ ለመስጠት ነበር። ግን በተማሪዎቹ አድማ ምክንያት፣መልስ የሰጣቸው አንድም አልነበረም። የሀገራቸው እንግዳ አምባገነን፣ "ውስጄ ሀገሬ ፍርድ ልስጥ" ሲሉ፣ ያገሩ መሪ ደግሞ "አድሜያቸው አይፈቅድም" ሲሉ፣ አምባገነኑ እንግዳ "ባገራችን፣ ወንጀለኛ ፍርድ አያስፈልገውም !" ሲሉ፣ ክርክር ገጥመው ከቆዩ በኋላ፣ እዚያው ባሉበት ከተማ እንዲቀጡ ተበይኖ፣ ዛሬም ሕፃናቱ ቅጣት ላይ ይገኛሉ። ሰመነ ግን፣ ከሀገሩ ሞግዚቷ የመረራቸው ቤተሰቦቿ ጋር፣ በዚያ ሰሞኑ የጀልባዎች ጉዞ፣ ወደ ጎረቤት ሀገር ከተሰደደች በኋላ፣ አሁን አውሮፓ ትገኛለች። የምትናፍቅ እናቷን ግን ዛሬም አላገኘችም !

____________***__________



# እናቴን ለመቅበር



አንድን ሕዝብ ለመግዛት፣ ዓይነተኛው ጥበብ፣
"መበተን፣ማራራት፣ ግንኙቱን ማጥበብ!"
ነው እሱ ሲታውንት፣ ያጠኑ ሥነ-ሕዝብ።

ከፋፍሎ ለመግዛት፣ ለገዥ እንዲያመች፣
ዕድሞ፣ ወሰን፣ አጥር፣ ያበጃል ሳይሰለች።

እናትን ከልጅዋ፣ ሳትወድ ይነጥላል፣
አንድ ላይ ካሉማ፣ ራሱም ይደግል!

ስለዚህኮ ነው፣ ይለፍ ፈቃድ ጠፍቶ፣
የማያፈናፍን፣ የውስጥ ደንብ ሠርቶ፣
ከርችሞ ወጥር፣ በሮቹን ዘጋግቶ፣
ፋሽስት የሚያስጨንት፣ ሕዝቦችን በላልቶ!

# መንደርደርያ

ማንኛውም የሰው ልጅ እንዲሁ እምኀበ-አልቦ፣ ከሰማያት በርቆ የተገኘ አይደለም። በጥምር ወላጆቹ አማካይነት፣ በሕገ-ተፈጥሮ የተወለደ ነው። በመሆኑም፣ የተወለደበት ሀገሩ፣ አፅመ-ርስቱና መብታዊ ቤቱ ነው። ግላዊ መናኸሪያው እስከሆነም ድረስ፣ የሌሎችን መብት ሳይጨነቁር እንደፈለገው የመኖርና የመዝናናት መብት አለው። በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ፣ የሚደክም እግሩ ይጭነቀው እንጅ፣ የመንቀሳቀስና የመጓዝ ነፃነት አለው። በሀገሩ ላይ በፈለገው ጊዜና ቦታ የመዘዋወር መብቱንና ነፃነቱን ምንም ዐይነት ምድራዊ ኃይል ሊያግርበትና ሊከረችምበትም አይገባም። የዚያ ሀገር ሰው ሆኖ የተገኘ ለታ፣ የተሰጠው የተፈጥሮ ልደታዊ ነፃነቱ ነውና !!

ታዲያንን፣ አለመታደል ሆኖ፣ አንዳንድ ጋጠ-ወጥ የዘመናችን የገዥ ቀንጮዎች የራሳቸውን ክብርና ገናናነት ያስከበሩና፣ የሕዝባችንንም የሕልውና መብትና ነፃነት እንደግል ችግሮታቸው የሚለግሡ እየመሰላቸው፣ በፈለጋቸው ሚና የሚነዱትን ሕዝብ፣ በገዛ ምድሩና በገዛ ሀገሩ ውስጥ፣ ከቦታ ወደቦታ በፈለገው ጊዜ እንዳይንቀሳቃስ አገረውት ይገኛል። ይህንንም ኢሰብዓዊ እገዳቸውን፣ በአዋጅና በልዩ ልዩ ኢሕጋዊ ትዕዛዛቸው በማጠናከር መዝናናት የተፈጥሮ ስጦታው የሆነውን ሕዝባችንን፣ እንዳይንቀሣቀስ አፍነውት እያወራጨት ነው።

በራሳቸው እምነት የሌላቸው፣ እሊህ ጥብጥ የማይሞሉ የገዥ ቡድናዊ መደቦች አካል፣ በዚያ ሕዝብ መሠረታዊ የመንቀሳቀስ ፍላጎቱ ላይ ሲያሾፍና

ሲቀልድ፣ ነበረም አለም። ይህ “የአትንቀሣቀስ” እገራ፣ ከድኅረ–የካቲት ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ላይ፣ ከወረዱት መዓቶች ውስጥ አንደኛው ነው። ነጋዴው ተዘዋውሮ እንዳይነግድ፣ ሞፈር ዘመቱ ገበሬ ተዘዋውሮ እንዳያርስ፣ ሕዝቡ ተዘዋውሮ ከወገኑም ሆነ ከዘመዱ ተገናኝቶ እንዳይወያይ፥ ... በማያፈናፍን አዋጅ ከርቸሞ፣ ሲያስጨንቀው ኖሯል፣ አለም። ይህች አጭር ልቦለድ ታሪክ፣ ይህን እፈና በማስመልከት የተነደፈችና ታሪካዊ ብልጭታነቷም ይህን አሠቀቂ፣ የሰብዓዊ መብቶች አንዱ የሆነውን ክፍል፣ ረገጣና እፈና የምታንፀባርቅ ጭላንጭል ናት።

ከነፃነት ዘርፎች አንዱ፣ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ያለአንዳች ሐሳብ፣ ቀልብ ሳይሠቅሉ፣ እንደልብ መዘዋወር መቻል ነው። በተለይም በገዛ ሀገር ውስጥ በራስ ምድር ላይ፣ የመጓጓዣውን ብርና የእግር ጣመን ይጭነቀው እንጅ ከፈለጉበት መካን፣ አምባ፣ ደብር፣ መንደር ግዛት ... መሔድ፣ ማደር፣ መንሻርሸር፣ የየአካባቢውን ነፃና ትኩስ ዓየር መተንፈስ፣ ተፈጥሮንም ተዘዋውሮ አይቶ ማድነቅ ... ትልቁ፣ ሰው የመሆን ነፃነት ነው። በተለይም የተለያየ መልክአ–ምድር ያላት ሀገራችን፣ በደጋ፣ በወይና አደጋ፣ በቆላ፣ በበረሐ፣ በባሕረ–ሸሽ ... የተከፋፈለች እንደመሆኗ መጠን ተዘዋውሮ ለመጎብኘት ማነኛውንም ኢትዮጵያዊ ያጓጓል። “የሚበላው ዳቦ የሌለው” አትበሉኝ እንጅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞኞቱ አንፃር፣ እንዲያ እንዲያ ነው። በተለይም ደግሞ፣ የታሪክ ቅርሶቻችን የሚገኙባቸው ሥፍራዎች በተለያዩ ክፍለ–ሀገሮች በመሆናቸው፣ “የእገራው አዋጅ” በመንቀሳቀስ እገዳው አንፃር ያለውንም ሌላኛ ተልእኮ ይጠቁማል። እነአኩስም፣ ላሊበላ፣ ጐንደር፣ ደብረ፥ዳሞ፣ ደብረ፥ ቢዘን፣ግሸን፣ መቅደላ፣ አንኮበር፣ አደሬ ጢቆ፣ ኑራ ሁሴን ... እዩን እዩን በሚሉበት ዘመን፣ “አትንቀሳቀሱ” ን፥ ምን እንዳመጣው ከሌላ ጉዳይ ጋር ማገናዘቡ ቀላልና አስቸጋሪም አይደለም።

በተፈጥሮ ታሪካዊ ትርዒቱም፣ የነአባይ፣ የነግቤ፣ የነኦሞ፣ የነዋቢ ሸበሌ፥ ...ገጽታ እጅግ የሚስብ መሆኑን የሚያውቅ ሁሉ ያውቀዋል። እንደገሙ ጎፋ ያለው “የእግዜር ድልድይም”፣ ሌላው እውቀትና ደስታ የሚያስገኝ የተፈጥሮ





ትንግርት የሚታይበት፣ የሚጎበኝ ቦታ ነው። ለእንደዚህ ዐይነቱ የመጎብኘት ፍላጐት፣ የመንቀሳቀስ ነፃነት መኖሩ ተቀዳሚና ወሣኝም ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በየዘመኑ በተፈፀሙ፣ የጦርነት፣ የመፍለስ፣ የጋብቻ፣ የሥራ ዝውውሮች፥ ... የተነሳ ብዙ የማኅበረ–ሰቡ አባሎች፣ በተለያዩ ክፍለ–ሀገሮች፣ እንደጨው ተበትነው ይገኛሉ። ሌላው ቀርቶ የአንድ ቤተሰብ አባሎች እንኳ፣ በየምክንያቱ፣ በየቦታው ተሠራጭተው ይኖራሉ። በቆየው የሀገራችን ልምድ መሠረት የቤተ–ዘመድና የወዳጆች ተዘዋውሮ መጠያየቅ ነባር ባሕል ስለሆነ ተገናኝቶ መጨዋወት፣ ፍላጐቱም፣ ግዴታውም፣ ምኞቱም ጭምር ነው። ባሕል ባስገኛቸው የጋብቻ፣ የልደት፣ የተዝካርና፣ በሌሎቹም የሐዘንና የደስታ ዝግጅቶች ከያሉበት ተሰባስቦ መገናኘት የነበረና ያለ ነው።

ይሁን እንጅ፣ ከድኅረ–የካቲት ጀምሮ በዐብዮት ስም፣ የጥቂት ገዥ ቡድኖችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል፣ የተለያዩ ቤተሰቦችም ሆኑ ወዳጆች እንዳይገናኙ በአዋጅ ተደንግጎ እንደተነጣጠሉ ቀርተዋል። “ነጣጥለህና ከፋፍለህ ግዛ” በዚህ መልኩ በድርጊት ሲገለፅ ቆይቷል። ናፍቆት ሲያቃጥለው ይኖራታል እንጅ፣ ፍቅረኛም ጓደኛውን፣ ልጅም እናቱን ... የማየት እድላቸው የመነመነ ነው። በእገራው ፀጥታ ውስጥ የገዥ መደቡ እንደፈለገው ይፈልላል፣ እስረሽ ምቺውንም እንዳጦፈው አለ። በአዲስ አባባ እንኳ የስዓት እላፊው አዋጅ ባስከተለው ጦስ፣ ከቀበሌ እሥር ቤቶች ቦታ ጠቧቸው በሠንዳፋና በከርቸሌ ታጭቀዋል። ...

በተፈጥሮው ነፃ ባሕርይ ያለው የሰው ልጅ፣ አንድ ቦታ ብቻ ታፍኖና ታጅሎ መኖር አይዋጥለትም። ይህ ዐይነቱ እገራም፣ ሰብዓዊ የመንቀሳቀስ መብቱን ይፃረርበታል። አካላዊ መዋቅሩ ሳይቀር የመንቀሳቀስ ባሕል ያለውና ሆነኝም ተብሎ የተሠራ ነው። ተጓዥ (ሎኮሞቲብ) ነው። ታዲያንን ሁልጊዜ ተለጉሞ መቀመጥ አይሆንለትም ከድኅረ–የካቲት ጀምሮ የምናየው ያገራችን አገዛዝ ግን፣ በተቃራኒው፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ “ልውሽ፣ ድርሽ፣ ፈቀቅ፣ ንቅንቅ...” የለም የሚል ነው። የዚች አጭር ልቦለድ ጭብጥ ይህን አሠቃቂ የሰው ልጅ መብት ረገጣ አሰመልክታ፣ በገጠር የሞቱ እናቱን ለመቅበር አንድ ከተማ የሚኖር

## መንደርደርያ

ኢትዮጵያዊ፣ ሔዶ ለመቅበር የደረሰበትን ጣጣ ፈንጣጣ በጨረፍታ ታትታለች። ይህን ኢሰብአዊ እፈና በሽንቁር ጭላንጭል ለማሳየት በመሞከሯ፣ ትልቁን የሰው ልጆች የመንቀሳቀስ መብት መደፈር የምታሳይ "የብልጭታ ነፀብራቅ" ናት መባሏም በዚሁ ባሕርይዋ ነው። ይቻትላችሁ።



# እናቴን ለመቅበር

"... ራሴን ከራሴ የበለጠ የሚያውቅ ሌላ ሰው እንደሌለ እምናለሁ። እኔ ራሴ እኔነቴን ለማወቅ ብዙ ዘመን እንደፈጀብኝ ተረድቻለሁ። የገዛ ራሴን ባሕርይና ዝንባሌ፣ የእኔነቴንም ጠባይ ለመመርመር ምን ያህል ጉልበትና ትዕግሥት እንዳስፈለገኝ ከኔ ውጭ የሚያውቅ የለም። አካባቢ ኃይሎች የነደፉብኝን ሥዕሎች ሳንፀባርቅ መኖሬ ግን፣ ካቅሜ በላይ በግዳጅ የፈፀምኩት እንጅ፣ በውዴታዬ እንዳይደለ አውቃለሁ። ብሎም አካባቢዬን በሙሉ በነፀብራቄ አልቀዳሁም። አለያማ፣ በሠካራም ኅብረተ–ሰብ መካከል አድጌ፣ ጥሩ ጠጭ በወጣኝ ነበር። በቅንዝረኛና በዘማዊ ኅብረተ–ሰብ ጭን ስር ተመንድጌ፣ የወጣልኝ ቅንዝረኛ በሆንኩ ነበር። በሌባና በቀማኛ ኅብረተ–ሰብ አካባቢ ጉልብቼ፣ ካራዳዎቹ ወይም ከካቤኖዎቹ ወይም ከደርጉቹ ጩልሌዎች የበለጥኩ መንታፊ በወጣኝ ነበር።

የራሴን ግላዊ ድክመቶች በሚገባ ባውቃቸውም፣ ድክመቶቼ ሁሉ እንዲያ እንዲያ የመሳሰሉት አልነበሩም አይደሉም፣ አይሆኑምም። የነቃሁ፣ የጠራሁ፣ ሙሉ ጨዋ ባልሆንም፣ የለየልኝ፣ የወጣልኝ ሙሉ ባለጌ እንዳልሆንኩ አውቃለሁ። ራሴን በራሴ የማውቀው፣ እዚህ ድረስ ቢሆንም፣ ሌሎች ስለኔ በሚሠነዝሩት አስተያየት እገረማለሁ። ደግነቱ የሚያሥቀኝ እንጅ፣ የሚያስከፋኝ አለመሆኑ ነው። የፈለገውን ያሰተያየት ገመድ ቢተበትብ፣ እኔን ሊሸብበኝ እንደማይችል አውቃለሁ። የፈለጋቸውን የመሠናክል ወጥመድ ቢኰለኩሉ፣ እኔን እንደማያደናቅፈኝ እምናለሁ።

አንዳንዴም ከንቱ ሙከራቸው ሁሉ ሲታሰብኝ፣ ስለራሴ ሳይሆን፣ ስለራሳቸው አዝናለሁ። እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች፣ እነዚያን መሰል አስተያየቶች ሲሠነዝሩ፣

የራሳቸው መነሻና የግላቸው አመለካከት አስገድዷቸው እንደሆነ ይታየኛል። ከምን ላይ ተነስተው፣ በምንስ አመለካከት፣ የሚለውን ሐተታዊ ጥያቄ ግን፣ ማንሳትና መተንተን ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለመረዳት ያስችላል። ኧረ ለመሆኑ፣ እንዲህ፣ የወለደችኝን እናቴን፣ ቢቻል አስታምሜ ባይቻልም ለመቅበር፣ የሚከለክሉ ጉዶች ከምን የፈሉ መዓቶች ናቸው? ..." እያለ ልቡን እንደሳተና አእምሮውን ነካ እንዳደረገው ሰው፣ እቤቱ የናቱን መርዶ ስምቶ፣ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ በእንቡዘ–ልብ የሚያነበንበው ትዝታ ነው።

እድሜው አቅመ–አዳም ቢደርስም፣ አልተዳረም። "ሚስትና ጉንፋን" እንዲሉ፣ አጣማጁን ማግኘት ተስኖት ሳይሆን፣ በየሰበብ አስባቡ ዘግይቶ ነው። ተምሮ፣ ሥራ አግኝቶ ቤት ሠርቶ፣ ቆሳቁሶች ተሟልተውለት፣ ለትዳር ዝግጅት ላይ ነበር። በተለይም፣ "ሠርግህን ሳላይ እንዳልሞት" እያሉ፣ ያስጠነቅቁት የነበሩ እናቱ፣ የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት እስኪጨርስ እንዲታገሡት ብዙ ጊዜ ይማጠናቸዉ ነበር። ኋላም ትንሽ ጥሪት ልያዝ፣ ጐጆ ልቀልስ፣ እያለ፣ የናቱን ጥያቄ ሳይመልስ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ነበር። ወላጅ አባቱ፣ ገና እሱ በሕፃንነቱ እንዳለ፣ ከዓለሙ በሞት ስለተለዩ፤ አንድ እናቱ፣ እንደ አባትም፣ እንደ እናትም ሆነው ስላሳደጉት፣ የናቱ ውለታ፤ የሰማዩን ያህል እንደሚከብደው ዘወትር ይሰማዋል። ስለዚህም ነበር፣ ትዳር መሥርቶ፣ ወላጅ እናቱንም ካሉበት ክፍለ ሀገር፣ አዲስ አበባ በማስመጣት ከቤተ–ሰቡ ጋር ባንድነት ለማኖር በማሰብ ላይ እንዳለ፣ ድንገት የናቱን መርዶ የሰማው።

ይህ አሳዛኝ ወጣት፣ አኖሬዎስ ይባላል። ይህን ስም ያወጡለት ወላጅ አባቱ ናቸው። ምን ማለት እንደሆነና ለምንስ በዚህ ሥያሜ እንደጠሩት፣ እናቱም ይሁኑ ራሱ የስሙ ባለቤት አያውቁም። ከትምህርት ቤቶችና ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መዝገቦች ላይ ሳይቀር፣ በይፋ ተመዝግቦ ሲጠራበት፣ ከሠላሣ ዓመታት በላይ አልፈዋል። የሚሠራው በተመረቀበት የንግድ ሙያ ተመድቦ፣ ከአዲስ አባበ ንግድ ምክር ቤት ነው። መኖሪያው ግን፣ በጭስኝነት ተመርቶ፣ በብድር ከሠራው፣ ከኰተቤ አካባቢ ነው። በዶሞዝ ሰሞን ብቻ የሚያመጣት አንዲት





ክርካሣ ቮክስ አለችው። ያውም ቢሆን፣ በጣም ሲነሽጠው እንጅ፣ በብዙ የደሞዝ ወቅቶችም ያላወጣበት ጊዜ አለ። ወረት ለሚፈጥሩ ብርቅዬ ነገሮች፣ በጣም ቁጥብ ነው። ባለባበሱም ሆነ ባኗኗሩ ግድየለሽ ነው። የፀደይ ልብስ የበጋ ልብስ...የሚሉ የየወቅቱ ልብሳዊ ዘዬዎች ትዝም አይሉት። ለወረት ተብሎ የሚደረግ ነገር ሁሉ፣ በሽታው ነው። ለጤናው በማሰብ እንጅ፣ ለውብት ሲል ፀጉሩን ያስተካከለበትም ሆነ ያበጠረበት ወቅት፣ ትዝም አይለው። ለናዚራ ስሜቶቹ የተንበረከከባቸው ጊዜዎች፣ በጣም ውሱን ናቸው። ተንኰል የሚባል ነገር፣ ሊያደርገው ቀርቶ ሌሎች ሲፈፅሙ ሲያይ፣ እጅግ ያዝናል። ከየዋህነቱ የተነሣ፣ ባልንጀሮቹ ሁሉ "በጐ" የሚል ሥያሜ ሰጥተውታል። የዋህ ይሁን እንጅ፣ የዋህነቱ ድንበር አለው። ጌታ በሎሌው ላይ ሲፈነጭበት፣ ሀብታም በደሀው ላይ ሲያፌጭበት ብልጡ በሞኙ ላይ ሲያሾፈበት፣ ከበርቴው በላብ አደሩ ላይ ሲጋልብበት፣ ጉልተኛው በገባሩ ላይ ሲሸናበት ... አጋጥሞት ባየ ቁጥር፣ ዛር የሠፈረበት ባለአዶ ከብሬ ይመስል፣ በንዴት ያንቀጠቅጠዋል። አንዳንዴም ሁኔታው አላስችል ብሎት ቡራከረዩ በማለቱ፣ ባለጉልበተኞች ይዘው "ቸብቸብ" የተደረገበት ወቅት ነበር።

ወጣት አኖሬዎስ፣ በበጐ ምግባሩና በሸጋ ባሕርዩ፣ የማያውቀው የጐረቤት ሰው የለም። ቅንነቱና የተገራ ጠባዩ ያለአባት ያደገ፣ አያስመስለውም። በወላጅ እናቱ ግለኛ ርዳታ ያደገ ቢሆንም፣ "ሴት ያሳደገው !" የሚያሰኝ ባሕርይም ሆነ ዝንባሌ አልነበረውም። ወላጅ እናቱም፣ አካባቢው ካስገኘላቸው ሥርዓት፣ በጐውን እየመረጡ ተጨንቀውና ተጠበው ነው፣ በእንክብካቤ ያሳደጉት።

"የእንጀራ አባት" ተግሣፅና በትር እንዳይደርስበትም በማሰብ፣ ሌላ ወንድ ሳያውቁ በብቸኝነት የኖሩትም ለአኖሬዎስ ልጃቸው ሲሉ ነው። ገና ሕፃን ሆኖ በባላገር ሳለ፣ ለእረኝነት ተግባሩ ወደተሠማራበት መስክ ድረስ በመሔድ፣ ምግብ ሲያቀርቡለትና መንፈስ–ጠንካራ እንዲሆን የሚያስችሉትን፣ የተለያዩ ተግባራዊ ምክሮችን ሲለግሡት ያያቸው ሰው ሁሉ፣ ላንድዬ ልጃቸው ምን ያህል እንደሚንሠፈሠፉለት ያውቅ ነበር። የሟች አባቱ ታናሽ ወንድም የነበሩ አጐቱ፣

የሚኖሩት ከመናገሻው ከተማ ስለነበር፣ አዲስ አበባ በጉልማሳነቱ ወራት አምጥተው ያስተምሩት ነበር። አጉቱም ቢሆኑ፣ እንደ ወላጅ አባቱ፣ በአፍላ ዘመናቸው በድንገተኛ አደጋ ስለሞቱበት፣ አኖሬዎስ አብዛኛውን የትምህርት ዘመኑን ሊቋቋምና ሊገፋ የቻለው፣ ልዩ ልዩ የጉልበት ሥራዎችን በመሥራትና ራሱን ያለንዳች ረዳት በራሱ ጥረት ብቻ በመደገፍ ነበር። በዚያ ረዥም ዘመናት ውስጥ፣ ለተወሰኑ ጊዜያቶች ብቻ ዕድል አግኝቶ፣ እናቱ ከሚኖሩበት የትውልድ ቦታው፣ ወለንጭጥ ብቅ ብሎ ጠይቋቸዋል። ትልቁ ዓላማው ግን ትምህርቱን ጨርሶ ሥራ እንደያዘ፣ ወላጅ እናቱን አዲስ አበባ አምጥቶ፣ ከሚበላው እያበላ፣ ከሚለብሰው እያለበሰ ለመጦር ነበር። ግን ታመው ሞቱ።

የወላጅ እናቱን ሞት መርዶ ሰምቶ፣ ሀዘን ላይ መቀመጡን ያወቁ፣ የወላጅ እናቱ የድሮ ጓደኛ የነበሩ አንዲት ጠጅ ነጋዴ እመቤት፣ ከሀዘኑ ተከፋይ ለመሆንና ለማፅናናት፣ ከሚኖሩበት ሠፈር፣ ከጉለሌ ይመጣሉ። ወትሮም ቢሆን የናቱ አደራ ስላለባቸው፣ አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ ይጠይቁት የነበሩ ናቸው። አኖሬዎስ ከመኖሪያ ቤቱ፣ ከጥቂት ጓደኞች ጋር ተቀምጦ በሐዘን ላይ እንዳለ እኝህ እመቤት፣ "እህቴ እህቴ ምን አገኘዎ !" እያሉ ደረታቸውን እየመቱና እያለቀሱ ይገባሉ። ያገር ደንብ ነውና፣ እቤቱ ውስጥ ያለው ሁሉ ልቅሶውን ተቀብሎ ካለቀሰ በኋላ፤ ለሴትዮዩቱ የሚያርፉበት መቀመጫ ይሰጣቸዋል። እመቤቲቱም ልቅሶአቸው ጋብ ካለ በኋላ፤

"አንተዬ አኖሬዎስ ! እኔን አፈር ይብላኝና፣ እንዲያ ሲንሰፈሰፉልህ ሞተው ይረፉ!"

"አዎን፣ ይኸውልዎ፣ አንድ እጅ ብቻ ነበረኝ፣ እሱንም ተቀረጥሁ"

"ለመሆኑ መቼ ነው ያረፉት !"

"ትላንትና ሣምንቷ አለፈ !"

"እንዴ ቆይቷልና !"

"እዎ ዘጠኝ ቀናት ሆነ !

"ለመሆኑ አንተ የሰማኸው መቼ ነበር ?"





"ገና በጠና ታማ ለመሞት ስታጣጥር ሳለች ነበር !"

"ታድያ ሔደህ አየኻቸው እንዴ ?"

"ሞክሬ አልተሣካልኝም !"

"ድራሼ በጠፋ! መሔድ አልቻልክም ?"

"እኔማ ምኞቴና ሐሳቤ፣ ሌላው ቢቀር፣ ማለቴ በክብር መጦሩ እንኳ ቢቀር፣ እዚሁ እኔውጋ አምጥቼ ለማስታመም ነበር ! እልሆነልኝም እልዎታለሁ !"

"ለመሆኑ ምን ዐይነት ዘመን ላይ ደረስን ይሆን ? ሰው ወላጅ እናቱን እንኳ ለማስታመም ያልቻለበት ቀውጢ ዘመን ! ኧረ ለመሆኑ የመሔጃ ፈቃድ ለማግኘት አመልክተህ ነበር?"

"እንዴታ ! እግሬ ብቻ ሳይሆን ጉረሮዬ ጭምር እስኪነቃ ድረስ ነበራ !"

"ምን መልስ ሰጡህ ?"

"ማዕከላዊው አመራር ውስጥ ጥያቄህ እየተጠና ነው" የሚል ነው !

"ጥያቄህ እንደተሠቀለ ሣለ ነዋ፣ እናትህ የሞቱት !"

"አዎን ! ያረፈችው ማመልከቻዬ ተንጠልጥሎ እንዳለ ነው !"

"እኔኮ በጣም የሚገርመኝ፣ ያሠራራቸው የጅራፍ ቀግ ያን ያህል ረዝሞ፣ መንዛዛቱና መንጆልጆሉ ብቻ ነው !"

"አዬ ይተውኝ እባክዎ፣እንደፈለጉ መጓዝ፣ በተመኙት አከባቢ ተንቀሣቅሶ መዝናናትም ሆነ፣ ጉዳይን ማከናወን ቀደም ቀረ !"

"ውነትህን ነው ! መላወስኮ አልቻልንም ! ድሮኮ ማር እንኳን ለመግዛት፣ በመርሐ ቤቴ ቀላና በጉጃም ገጠር ሳይቀር፣ በየሣምንቱ እየተመላለስንበት ነበር! ዛሬ እዚሁ ከተማችን ውስጥ እንኳ፣ የበሌው እንጠጦ፣ የገፈርሳው ኩተቤ መዘዋወር አልሆነለትም ! ያሳዝናል !"

"በተለይማ፣ ይህ እኔ የምኖርበት ቀጠናና ቀበሌ፣ እንደ አንዳንዶቹ ቀበሌዎች፣ ያድኃርያን ቀበሌ የሚል ስም ስለተሰጠው፣ ያለው ቁጥጥርና ክትትል፣ በጣም ጥብቅ ነው። የቀበሌዎቹ ሹሞችና ዐብዮት ጠባቂዎች ጭምር በአድኃርያን መልክ

ስለሚታዩ፣ የቀበሌው ነዋሪ ለሚያቀርበው ማመልከቻ ሁሉ፣ ውሣኔውን የሚያገኘው፣ ከሌላ የተራማጅ ቀበሌ በሚመጡ ሹማምንት ነው።"

"ምን የናንተ ቀበሌ ብቻ ! የየትኛውም ተመሳሳይ ነው። በየምሽቱ እኔጋ የሚመጡ፣ የየቀበሌው ሰዎች ሁሉ ሲያማርሩ ሰምቻለሁ !"

"ምን ማለትዎ ነው ! ማን ያልተቸገረና ግራ ያልገባው አለ ብለው ነው ? የማያፈናፍኑ ድርጊቶች እየደረጁና እያደጉ በመምጣት ላይ ናቸው።"

"ምን በመምጣት ላይ ናቸው ትላለህ ! መጥተዋል እንጅ ! ወላጅን ከልጁ፣ ሚስትን ከባሏ፣ ዘመድን ካዝማዱ ሲያራርቀውና ሲለያየው እያየን ! እንዲያማ ባይሆን ኖሮ፣ አንድ ወላጅ እናትህን መቅበር፣ መች ያቅተህ ነበር ! ምን አንተ ብቻ ! እኛ ሁላችንም ተገኝተን፣ በሥርዓት በሸኘናቸው ነበር !"

"እዬ ይተውኝ፣ አንጀቴኮ ነው የተቃጠለው !"

"እንተ እንኳ፣ ክፋት የማታውቅ፣ ተንኮል የሌለብህ ሰው ነበርክ ! እንዴት ሊከለክሉህ እንደቻሉ ገርሞኛል !"

"ምን መከልከል ብቻ፣ አንከራተቱኝ እንጅ ! እዚህ፣ አንዴ ቀጠና ሹምጋ፣ አንዴ ቀበሌ ሹም ዘንድ፣ አንዴ ዐብዮት ጠባቂዎችጋ፣ ከዚያ ደግሞ ከፍተኛ ዘንድ የተንገላታሁባቸው ሰዓቶች ጥቂት አልነበሩም። ከዚህ እንዳለቀልኝ፣ ደረቅ ጣብያ በማበል ከታወቀው የትውልድ ቦታዬ ለመድረስ፣ በየጣ ቢያው ያልደርሰብኝ ፈተና የለም። ከአቃቂ ጀምሮ እስከ ናዝሬት ለመድረስ አራት ቀናት ፈጅቶብኛል።

አንዴ የመታወቅያ ወረቀቴ በቂ አይደለም ስባል፣ አንዴ፣ ለማስተላለፍ የበላይ ትዕዛዝ እንጠብቃለን ስባል፣ የኋላ ኋላ መጨረሻ ላይ፣ በናዝሬቱ ከተማ የፓሊስ አባሎች፣ ወደ ወለንጪቲ የምጓዝበት ጉዳይ የሚያስጠረጥር መሆኑ ተነግሮኝ፣ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ እንድመለስ ተደረገ። የትውልድ ቦታዬ፣ ወለንጪቲ መሆኑ እየታወቀ ወላጅ እናቴ በዚያ መኖሯ እየተረጋገጠ፣ በተለይም በአሐዜ ዓለም ተይዛ ለሞት በማጣጣር ላይ በመሆኗ፣ ያስቸኳይ መልእክት ማስተላለፉ እየታወቀ፤ "የወለንጪቲ ጉዞህ ያስጠረጥራል ..." ሲባል፣ የተሰማኝ ንዴትና ብሽቀት መግለጫ አላገኝለትም። ደግነቱ፣ ብሽቀቴ ለተወሰኑ ደቂቃዎች





ያህል ሲያርበተብተኝ ከቆየሁ በኋላ፣ ቀኑን ሙሉ ደብተኝ መዋሉ ብቻ በጀኝ እንጅ፣ ጤናማና ንቁ ብሆን ኖሮ፣ በራሴም ላይ ሆነ በሌላ ሰው ላይ፣ የከፋ እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ አልልም ነበር ??

"አይ ልጄ ! መታገሥ ነው እንጅ፣ መናደዱማ ምን እርባና ይኖረዋል ብለህ ነው ?"

"ኧረ ይተውኝ ! በናት ሞት ላይ የሚደረግ ትዕግስት፣ ምን ረብህ አለው ብለው ነው ? የኔ ጅልነት ማርኩኝ፣ ወይም ለመኖር ያለኝ ፍላጐት አሸንፎኝ፣ ይሆናል እንጅ፣ በገዛ ሀገሩ፣ በገዛ ወገኑ፣ በገዛ ምድሩ ... ለሚኖር ዜጋ፣ ብሔራዊ ክብሩን ተገፎና፣ ሰብአዊ ነፃነቱን ተነፍጐ፣ እየተሸማቀቀ ከመኖር የበለጠ፣ ምን የከፋ ሌላ ውርደት ሊያጋጥመው ይችላል ? በዚህ ዓይነቱ ህላዌ ሲንገላጀጁና ሲያደዘድዙ ከመኖር ይልቅ፣ አለመኖር ይመረጣል። በሕይወት መጨማለቁ፣ በተፈጥሮው ክቡር ለሆነ ሰው፣ ምርጫው አይደለም። የሚቻል ከሆነ፣ ሊለወጥ የሚችልበትን ዘዴ መሞከሩ ያዋጣል። አለያም፣ አንዳንድ ቀራጥ ወገኖቻችን ያሳዩንን አርአያነት፣ መከተል ይኖርብናል። የነ አቶ ዘካርያስ ጉዳና፣ አማራጭ የሌለው ጥርጊያ መንገድ ነው። በተጓዘበት መንገድ መከተል፣ በውርደት ከመኖር ይልቅ፣ በክብር መሞትን ያስገኛል ! በርግጥ ከነአቶ ዘካርያስ ቀራጥነት፣ መማር ይኖርብናል። አይመስላችሁም እንዴ ወንድሞቼ ?" ሊያስተዛዝኑት የተቀመጡቱን ጓደኞቹን ይጠይቃል።

"እነ አንተዬ፣ አቶ ዘካርያስ ደግሞ ማን ነው ?" አሉ እንግዳዋ ወይዘሮ።

"እዚሁ ኩተቤ የሚኖር ጐረቤታችን ነበር !" አለ ከጓደኞቹ አንዱ ፤

"ምን ያጋጠመው ይሆን ? ያልስማነው ትንግርት በየሠፈሩ ሞልቷልእኮ !"

"በደረሰበት ችግር ተበሳጭቶ፣ ያበሳጩትን ይዞ ያለፈ ነው !"

"መቸ ይሆን ይህ ደግሞ የተፈፀመው ?"

"ሦስት ወራት ያህል አልፎታል !"

"የማይደረግ ነገር የለም! ምን ነበር የተፈፀመበት ?"

"እዬ! የሱማ ሁኔታና የተፈፀመበት ግፍ ያሳዝናል !"

"ምን የማይፈፀም ግፍ አለ ብላችሁ ነው !"

"በሱ ላይ የደረሰው የተለየ ነው። ... በዚያ፣ አዋጅ በየቀኑ ይፈስ በነበረበት ወቅት ነው። የሚሠራው ትልቅ ኃላፊነት ያለበት የኢንጅነርነት ሥራ ነበር። ምድብ ሥራው ዐየር መንገድ ነው። ቦሌ ! እሱ መብረር ይችላል ብሎ ውሣኔውን በፊርማው ያላፀደቀለት ጄት አሮፕላን ሁሉ፣ ከቦታው መንቀሣቀስ አይችልም። ታዲያ በዚያ ሰሞን በአንድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ ሁለት የተለያዩና እርስበርሳቸውም የሚቃረኑ ተፃራርያን አዋጆች ይወጡ ነበር።

አንድ ዕለት ቀኑን ሙሉ "የየትኛውም መሥሪያ ቤት ሠራተኞች፣ በምድብ የሥራ ጊዜያቸው ወቅት፣ በምድብ ሥራቸው ላይ የማይገኙ ቢሆን፣ እንደ አድኃርያንና እንደ ፀረ–ዐብዮተኞች ተቆጥረው፣ ከፍተኛ ዐብዮታዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል" የሚል አዋጃዊ ማስጠንቀቂያ ሲነገር ይውላል። በዚያኑው ዕለት፣ ማታውን ደግሞ "ፀረ–ዐብዮተኞች፣ የፖለቲካ አሻጥር ለመፈፀም ስለተደረሰባቸው፣ በቁጥጥር ሥር ለማዋል፣ በሚወሰደው እርምጃ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣ ነገ ማንኛውም ተሽከርካሪ ካለበት ቦታ እንዳይንቀሳቀስ !" የሚል ሌላ አዋጅ ይወጣል። አቶ ዘካርያስ ከዚህ ከኩተቤ መኖሪያ ቤቱ፣ ለሚመለከተው የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ ስለሁኔታው በተቀዳሚ በስልክ ከነገረ በኋላ፣ መኪናውን ከቤቱ አስቀምጦ ረዥም ጉዞውን በእግሩ ይይዘዋል።

የዕለቱ በራሪ ጄት አውሮፕላኖች ሁሉ፣ አቶ ዘካርያስ፣ ቦሌ እስኪደርስ ድረስ፣ መጠበቅ ነበረባቸው። ልዩ የመጓጓዝ ፈቃድ የነበራቸው የውጭ ሀገር መንገደኞችም፣ ያለውዴታቸው፣ ያቶ ዘካርያስን መድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በእግር መጓዝ ልምድ ያልነበረው አቶ ዘካርያስ፣ የሁለት ሰዓት ጊዜ ያህል፣ ከምድብ የሥራ ሰዓት ጊዜው ዘግይቶ ይደርሳል። የሚጠበቅበትን ተግባር አከናውኖ፣ የዕለቱ መንገደኞች ጉዞአቸውን ከቀጠሉ በኋላ፣ አቶ ዘካርያስ፣ በምድብ የሥራ ሰዓት ጊዜው፣ በወቅቱ አለመገኘቱ፣ ሌላ አሻጥር ሲያከናውን ነው፣ በሚል ግምት አስጠርጥሮት፣ ወዲያው ለምርመራ፣ ወዳልታወቀ የቀበሌ





ከፍተኛ እሥር ቤት ይወሰዳል። ከዚያም ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር ያህል፣ የት እንደደረሰ የሚያውቅ ሰው አልነበረም።

ወሩን ጨርሶ እንደተለቀቀ፣ ስምንት ቀን ባልሞላው ጊዜ ውስጥ፣ አስፈላጊውን ግላዊ ዝግጅት አድርጎ፣ አንድ ወር ታስሮ ሲማቅቅ ወደ ነበረበት አካባቢ ሔዶ፣ በጊዜው የነበሩትን የቀበሌውን ባለሥልጣኖች ከረፈረፈ በኋላ በመጨረሻ ላይ፣ በያዘው መሣሪያው ራሱን ያጠናቅቃል። እንዴውም በሠፈራችን ዘካርያስ የሚለው ሥያሜ ተረስቶ "ሣልሳይ ቴዎድሮስ" ነው የሚባለው !"

"በቃህ ! በቃህ ! ልጄ። ብሶት ለያዘው ሰው፣ ማጭድ አታውሰው ! አኖሬዎስ ወጣት ልጅ ነህ። ተድረህ፣ ተኩለህ፣ ገና ዓለምህን አላየህም። በስንት ሥቃይ ስትማር ኖረህ፣ ገና አሁን ሥራ መጀመርህ ነው። ሁኔታው ቢያሳዝንም የሞቱትን እናትህን እንደገና በሕይወት ማግኘት አትችልም። ሀዘንህን ዋጥ አርገህ፣ ኑሮህን መመሥረት ይኖርብሃል። በወረደብን መዓት፣ በየቤቱ ያልቆሰለና ያልነደደ ሰው አይገኝም። ርግጥ ፍቃድ አግኝተህ፣ እናትህ ካሉበት ሔደህ አስታመህ ብትቀብራቸው ኖሮ፣ ሀዘንህ በመጠኑም ቢሆን ይከፈልልህ ነበር ! ይኸ መቸም ቀላል ሠቀቀን አይደለም ! ግን ምን ያረጓል ! እናንተም ጓደኞቹ ምከሩት ! አፅናኑት ! የፈሠሰ ውሃ አይታፈስም !!

"ሌላው ቢቀር፣ አስከሬኗ የወደቀበትን መቃብሯን፣ ሔጄ ማየት አለብኝ !"

"እሱማ ያደርሰሃል፣ ቀስ ብለህ እንደገና አለስልስህ መጠየቅ ትችላለህ። ማመልከቻህን ስትፅፍም የልመና ቃና ያቤቱታ ሽታ፣ አክልበት። እንዴው በደረቁ፣ እንድሔድ ይፈቀድልኝ ብቻ ብትላቸው፣ ደስ የሚላቸው አይደሉም። ስምተኸኛል ?"

"አዩ ! እርስዎ ቢቸግርዎና ቢጨንቅዎ ነው እንዲህ የሚሉኝ ! ኧረ እኔ በመለማመጥ ነበር፣ ፊትም የደፍኩላቸው ! አያምኑኝ ይሆናል ! ማመልከቻዬን፣ አሁንም ቢሆን አልጣልኩትም ! ይኸውልህ ! እስቲ ይስሙት አንብላቸው ! (አጠገቡ ላለ ጓደኛው ወረቀቱን ይሰጣል)

"እኔ አምንሐለሁ። እነሱ የሚፈልጉትን ዝንባሌ ለመግለጥ ያህል ነው። በደንብ አውቃቸዋለሁ። በየምሽቱ እኔ መጠጥ ቤት ይመጡ የለም ! የየትኛውም ቀበሌ ቢሆኑ፣ ጠባያቸው አንድ–ወጥ ነው !

"ላንብልዎ ! የፃፈው ማመልከቻ እንዲህ የሚል ነበር !"

... ለኰተቤ ቀበሌ ሊቀ መንበር፣

የተለመደው ዐብዮታዊ ሰላምታዬ ይቀርባል።

ጓድ ሊቀ መንበር እንደሚያውቁትና እንደሚያምኑበት ሁሉ፣ ለማንኛውም ሰው፣ ከዐብዮትና ከሕዝብ ቀጥሎ የወላጅ እናት ፍቅር ይኖረዋል። በተለይ እኔ፣ በወላጅ እናቴ ላይ ያለኝ ፍቅር፣ እጥፍ ድርብ ነው። ሌላውን መዘርዘር ባያስፈልግም፣ ያለአባት ያሳደገችኝ እናቴ፣ ልዩ ፍቅር ልታሳድርብኝ የበቃች፣ ባለውለታዬ ናት። ከዛሬ ነገ ተሚልቶልኝ፣ እጠራታለሁ እያልኩ ስመኝ፣ ካለፈው ወር ጀምሮ፣ በጠና ህመም ላይ መገኘቷንና፣ ብዙም ቀን ልትቆይ፣ አቅም የማይኖራት መሆኗን በመግለጽ፣ መልእክት አስተላልፋልኛለች። ጓድ ሊቀ መንበር የሚያውቁኝን ያህል፣ በአብዮታችን ላይ፣ ምንም ዓይነት ደባ ያልፈጸምኩ፣ ነፃ ሰው መሆኔ ተገልጾ፣ እናቴ በሕመም ላይ ከምትገኝበት፣ የትውልድ ቦታዬ ሔጄ እንድጠይቃት፣ አስፈላጊው ፈቃድ እንዲሰጠኝ አመለከታለሁ። ..." የሚል ነው።

"እናት፣ ሀገር እንጅ፣ ወላጅ አይደለችም ብለውህ ይሆናላ !"

"ይቆዩኝ ! ይኸውልዎ፣ ለማመልከቻዬ የተሰጠኝ ምላሽ! አንብላቸው።"

"እባክህን የሚሰጡትን መልስ አውቀዋለሁ ! ከማር የጣፈጠ መሆን አለበት ! ችግሩ ግን ማስፈጸሙ ላይ ነው !"

"የተጻፈለት የፈቃድ ደብዳቤ የሚከተለው ነበር።" አለ ጓደኛው እያነበበ ...

ለሚመለከተው ሁሉ

በያሉበት፣

ለብዙ ዘመናት የደለበን ነባር አስተሳሰብ፣ በአንድ ውሱን ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ እንደማይቻል ሁሉ፣ አንዳንድ ግለ–ሰቦች የሚያንፀባርቁትን፣





የኋላ ቀር ባሕልና የመንፈስ ዝንባሌ ለመቆጣጠር፣ ጊዜ እንደሚያስፈልግ የታወቀ ነው። በቀበሌያችን የዐብዮት ተግባራዊ ሥምሪታችን ላይ፣ የጊዜው አስቸጋሪ የአሠራር መሠናክል እየሆኑ ከሚያጋጥሙን ነገሮች ውስጥ፣ ሠርግ አለብኝ፣ ተዝካር ላውጣ፣ ዘመዴን ልጠይቅ፣ ... እያሉ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር፣ በየጊዜው በማመልከቻ የሚጠይቁን ግለ– ሰቦች ሁኔታ ይገኝበታል። ዐብዮታችን እየተጧጧፈ በመጣበት በአሁኑ ወቅት፣ ፀረ–ዐብዮተኞችና አድኃርያን፣ እንዲህ ያለውን ጥያቄ መከታ በማድረግ፣ ልዩ ልዩ አሻጥሮችን መሥራታቸውም አይዘነጋም። በዘመነ–ዐብዮትም፣ የዘመድ ጥየቃና የመሳሰለው ተግባር ሁሉ፣ ተቀዳሚነት የሚሰጠው ጥያቄ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም የቀበሌያችን ነዋሪ የሆነው አቶ አኖሬዎስ፣ የናቱን መታመም በማስረጃ ጭምር ስላቀረበና፣ ከዚህ ቀደምም በቀበሌያችን የፈፀመው ምንም ዐይነት ወንጀል ያልተመዘገበና፣ ፀረ–ዐብዮት ድርጊት ያልሠራ ስለሆነ፣ በሸዋ ክፍለ ሀገር፣ በየረርና ከረዩ አውራጃ፣ በወለንጭቲ ወረዳ፣ በቀበሌ ሦስት የሚገኙትን እናቱን፣ ለተወሰነ ጊዜ ጠይቋቸው እንዲመጣ፣ አስፈላጊው የመተላለፍ አብዮታዊ ትብብር እንዲደረግለት እንጠይቃለን። ሆኖም ፀረ–ዐብዮተኞች ሁሉ፣ እውነተኛ ገፀ–ባሕርያቸው እስካልተከሠተ ድረስ፣ ሥውር መሆኑ እውቅ ነውና፣ ይህ የቀበሌያችን ነዋሪ በሚዘዋወርበት ሁሉ፣ አስፈላጊው ቁጥጥር ላልተ፣ የሚፈፀመው ወንጀል ቢኖር፣ ኃላፊነቱ የማይመለከተን መሆኑን፣ በበኩላችን አስቀድመን እንገልፃለን።

ከዐብዮታዊ ሠላምታ ጋር !

"አላልኳችሁም ! እንዲዘዋወር ፈቅደንለታል ካሉ በኋላ፣ ለሚፈፅመው ሌላ ወንጀል፣ ኃላፊነቱ አይመለከተንም የሚለውን ሐሳብ ምን አመጣው ! የሌሎቹስ ቀበሌዎች ሹሞች፣ ምናቸው ሞኝ ነው ! በበኩላቸው እነሱም መዘዋወሩን ቢከለክሉት፣ ጥፋታቸው ከምን ላይ ነው ? "ሥጋውን ሰጥተው፣ ቢላዋውን ከለከሉት" እንደሚባለው አይደለም እንዴ አሠራራቸው !! እንዴው አያድርስ

ብቻ ! አያጋልጥ ማለት ይሻላል እንጅ፣ ውልፍት ከማያስኝ ዘመን ላይ ነው የደረስነው !

እኔ እዚያ ጠጅ ቤቴ ሆኜ፣ በየቀኑ የማልሰማው የብሶት ዐይነት የለም። ግማሹ ከከተማ ባላገር ሔዶ፣ ግማሹ ደግሞ ከባላገር ወደ ከተማ መጥቶ፣ የቀረውም ካንዱ ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ሔዶ፣ ያልደረሰበትና ያላጋጠመው ትንግርት አይገኝም። የዘመድ መጠየቁን ጉዳይ ትተን፣ በሥራ ምክንያት እንኳ፣ የሚዘዋወሩ ሰዎች የሚደርስባቸው ፍዳ፣ የቱን ያህል የሚያሠቅቅ ነው።

ትዝ ይለኛል፣ በዚያ ሰሞን፣ አንድ ከጉንደር የመጡ አረጋዊ አዛውንት፣ ቤቴ ጠጅ ሊጠጡ መጥተው፣ እንደ ሕፃን ልጅ እያለቀሱ ያጫወቱኝ ብሶት፣ አንጀቴን ነበር የበላው። ያንድ አውራጃ ዳኛ ናቸው። እዚህ ካለው የፍርድ ሚኒስቴር የሚያስመጣ፣ የሥራ ጉዳይ አጋጥሟቸው፣ አስፈላጊውን ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር የሚያስችሉ ማስረጃዎች ይዘው፣ አዲስ አበባ ይመጣሉ። ብታዩዋቸውእኮ፣ ለዓይን የሚከብዱ አዛውንት ናቸው። ታዲያንን አዲስ አበባ እንደደረሱ፣ የሚያርፉበት ሆቴል ይፈልጉና፣ መርካቶ ውስጥ ያገኛሉ። ማንነታቸውን ማረጋገጥና ስለ እንግዳውም ለቀበሌው ሹም መግለጫ መስጠት ግዴታው ስለሆነ፣ የሆቴሉ ባለንብረት ለቀበሌው ይነግራል። ራታቸውን በልተው ሊተኙ ሲዘጋጁ፣ የቀበሌ የዐብዮት ጠባቂዎች ይደርሱና፣ አዛውንቱ መታወቂያቸውን እንዲያሳዩ ይጠይቃሉ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ የመ/ቤትዎ መታወቂያ፣ ከቢሮ ሰዎች ጋር በመመሣጠር የተገኘ ይመስላልና፣ የሚኖሩበትን የቀበሌ መታወቂያ እንፈልጋለን ይሏቸዋል። አዛውንቱ ዳኛ ግን፣ የመ/ቤታቸው መታወቂያ ብቻ በቂ መስሏቸው፣ የቀበሌያቸውን የነዋሪነት መታወቂያ አልያዙም ነበርና፣ በቀጥታ ወደ ቀበሌው እሥር ቤት ይወስዷቸዋል።

ጐንደር ያለው ቤተሰባቸው፣ አዲስ አበባ ናቸው ይላል። ያዲስ አበባው ዋና መ/ቤታቸው፣ ጐንደር ናቸው ብሎ ያስባል። አዛውንቱ ዳኛ ግን በመሐል የት እንዳሉ ሳይታወቅ፣ ለ40 ቀኖች ያላስታዋሽ በቀበሌ መህኒ ቤት ይማቅቃሉ። የኋላ ኋላ፣ አብሯቸው ታስሮ የነበር ሰው፣ ከቀበሌው ሲለቀቅ፣ ፍርድ ሚኒስቴር





ሔዶ፣ ስለሁኔታቸው በመንገሩ ብቻ፣ ሊፈቱ መቻላቸውን፣ እንባ እየተናነቃቸው አጫውተውኛል። ታዲያ ይኸንን ምን ትሉታላችሁ ? አያድርስ ! አያጋልጥ ነው እንጅ! አሉ ወይዘሮ በረዥሙ እየተነፈሱ።

"ፈረንጆች ፓሊስ-ስቴት" ነው ብለው የሚጠሩት፣ እንዲህ ያለውን፣ የዜጐችን ነፃነት የሚነፍግ፣ ዜጐችን የማያላውስና የማያፈናፍን ሥርዓት ያለበትን ሀገር ሁሉ። የኛም እንደዚያው መሆኑ ነው። ይሁን እንጅ፣ በተፈጥሮው ነፃ የሆነን የሰው ልጅ፣ በተወሰነ ቦታ ብቻ ከርችሞ ለማቆየት መጣር፣ ዘለቄታ የሌለው ሙከራ ነው ! ..." አለ ከአኖሬዎስ ጓደኞች አንዱ

" አዩ እሱማ ! የታፈነ ሁሉ መፈንዳቱ፣ ተራ የተፈጥሮ ሕግ አይደለም እንዴ !" ይላል ሌላኛው ጓደኛ፣ ድጋፉን በመስጠት።

"ልክ ናችሁ። ግንኮ የታፈነው እስኪፈነዳ ድረስ፣ ብዙ ሰው ማቀቀ ! የኔም እናትኮ፣ ከማሕፀኗ የተገኘው ልጇ እንኳ፣ ላንድ ቀን እድሜ ሳያስታምማት፣ በባዶ ቤት ብቻዋን ማቅቃ ሞተችኮ ..." ይልና አኖሬዎስ ለቅሶውን ያቀልጠዋል፣ የወላጅ እናቱ ትዝታ አንጀቱን እያቃጠለው።

"ልጄ ታገስ ! ልቅሶውም ይበቃኻል ! ባፈናው ምክንያት፣ የቅርብ ረዳታቸው ሳይደርስላቸው የሞቱት፣ ያንተ እናት ብቻ አይደሉም ! በየቦታው ብዙ ባይተዋር እናቶችም እንደሚሞቱ፣ ማዘከር ይኖርብሃል። ራስህን በራስህ አፅናንተህ ለመኖር መሞከር ይኖርብሃል። የናትህን ሞት እያስብክ፣ ሆድ እንዲባባህ ማድረግ የለብህም። ወጣት ስለሆንክ፣ ገና የትዳር አለም ይጠብቅሐል። ተበረታተህ መቋቋም ግዴታህ ነው !!" እያሉ የሟች እናቱ ጓደኛ በመምከር ላይ እን ዳሉ፣ ከውጭ ሁለት ሰዎች ይገባሉ። መቀመጫ ተሰጥቷቸው እንደተቀመጡ የተለመዱ የሀዘን ቤት ጥያቄዎች ይደረደራሉ።

"ብዙ ታመው ነበርን ? ምን ሕመም ነበር ? እድሜያቸው ገፍቶ ነበር ?" አስፈላጊውን ምላሾች ከሀዘንተኛው አኖሬዎስ ካገኙ በኋላ፣ ትችት ይጀምራሉ።

"መቸም አቶ አኖሬዎስ፣ እንደምታውቀው ሁሉ፣ በዐብዮት ላይ የሚገኝ ሕዝብ፣ እንዳለፈ የጉልተኛና የከበርቴ ዘመን፣ ለልቅሶና ለሀዘን ሥርዓት ጊዜ አይኖረውም። ዓላማውም ሆነ ግቡ፣ ካለው ሁኔታ ላይ ተነስቶ እውነታን በመጨበጥ፣ ትግል ያከናውናል እንጅ፣ ባለፉ ነገሮች ላይ ሙጥኝ ብሎ፣ ጊዜ ማጥፋት አይኖርበትም። ደግሞም እንግዳ ዐብዮታችንን፣ በሚገባ ለማስተናገድ እንድንችል፣ ከስሜት ጋር የተያያዙ ትንንሽ ነገሮችን መርሳት ይኖርብናል። ዐብዮት እስካለ ድረስ፣ ያለና የሚኖር ነገር ሁሉ፣ ሕያውነቱ ዋስትና አለው። ስለዚህም ሙታንን መርሳት ይኖርብናል ..." ብሎ እንደኛው ሊያስተዛዝን የመጣ እንግዳ ሲያበቃ፤

"እናቴን አልረሳም !" ብሎ ለመናገር አኖሬዎስ ብልጥ ብሎበት ነበር። እነዚህ አስተዛዛኞች እነማን እንደሆኑ ስለሚያውቅ፣ እየተፈላሰፉ የተለፋደፉበት ምክር ማርኩት ሳይሆን፣ ስላለፉ ነገሮች ማዘን አለማስፈለግ፣እውነተኛው ትርጉምና ፅንሰ-ሐሳብ ተሰምቶት፣ ሊያወጣው የነበረውን የተቃርኖ ምላሽ፣ እንደምንም ውጦ፣ ዝም አለ። እነዚያም ሁለት የቀበሌ የዐብዮት ነፍጠኞች፣ አኖሬዎስን ለማስተዛዘን ብቻ ሳይሆን፣ ከላይ የተጠቀሰውን መለእክት ለማስተላለፍ ሲሉ፣ የተወሰኑ ደቂቃዎች ከተቀመጡ በኋላ "በሀዘን የሚፀፀት ልብን፣ በዐብዮት መንፈስ ማደንደን ነው!" የሚል "ፅናቱን ይስጥህ" እንደማለት ያለ የመስናበቻ ቃል ወርውረው ይወጣሉ። ገና እግራቸው የበሩን ዳጃፍ ረግጦ እንደወጣ፣ ድምፃቸውን አጥፍተው፣ ጭጭ ብለው የነበሩት፣ እኛ ሴት ወይዘሮ፤

"እነዚህ እንግዲህ፣ የቀበሌያችሁ ሹሞች መሆናቸው ነው !" አሉ።

"አዎ የበታች የቀበሌ ሹሞች ናቸው !" አለ አንዱ ያኖሬዎስ ጓደኛ።

"አሁንኮ የነሱ እናት ቀርቶ፣ ውሽማቸው እንኳ ብትሞት፣ ድንኳኑ ሳይቀር ተጥሎ፣ ስምንት ቀን ሙሉኮ ነው፣ ድግስ ቤት ይመስል ሽብ ረብ ሲሉ የሚከርሙት !" አሉ ተቆጥተው።

"የዘመናችን የቀበሌ ደጃዝማቾች አይደሉ ብለው !" አለ እያሽሟጠጣቸው።

"ታዲያ እነሱ የማያደርጉትን፣ ለምን ለሌላ ያስተምራሉ ?" አሉ ሴትዮዋ።





"የራስና የሌላ የሆኑ ነገሮች ሁሉ፣ ለየቅላቸው አይደሉ ብለው ?" አለ እንደኛው ጓደኛ።

"በጣምኮ የሚገርሙ ትንግርቶች ናቸው ! አላጨወትኳችሁምኮ መሰለኝ ! ያ የኔ ጠጅ ቤት ያላሳየኝ ጉድ የለምኮ ! እንደምታውቁት፣ በሥራ ሰዓት መጠጥ ቤቶች ዝግ ናቸው። ታዲያንን፣ እነሱ ሹልክ ብለው በአሳቻ ሰዓት በጓሮ በር ገብተው፣ ሲጠጡ ነው የሚውሉት።

"ታዲያ አንዳንድ ቀን፣ የጉረቤት አንዳንድ አዛውንቶች፣ በተለይም ጡረታ የወጡ አዛውንቶች ቀኑ እየረዘመ ሲያሰለቻቸው፣ እንደነሱው ተደብቀው መጥተው ሲጠጡ ይውላሉ። የሚገርመው፣ እነዚህን አዛውንቶች እነሱ ራሳቸው ተደብቀው ለመጠጣት ሲመጡ ያገኟቸው እንደሆነ፣ ወዲያው አቻኩለው፣ ፎቶግራፍ አንሺ ያስመጡና፣ ጠጅ በጠርሙስ ሙሉ ይሉንና፣ የጠርሙሱን ጠጅ ራሳቸው ላይ አስቀምጠው ፎቶግራፍ እያነሱ፣ በጋዜጣና በቴሌቪዥን ለሕዝብ እንዲታዩ ያደርጓቸዋል። ማዋረድ ያሉት ነው። በዚህ ድርጊታቸው ስንቱን አዛውንት እንደ አሻንጉሊት እያደረጉ ተጫውተውበታል ! እነሱ ግን ከዕለት ዕለት፣ በግላጭ እየመጡ፣ በጠራራ ፀሐይ ሲጠጡ ሲውሉ፣ ሌላው ቀርቶ የጠጡበትን ገንዘብ እንኳ የማይከፍሉበት ጊዜ አለ። ታዲያ እኔ የሚገርመኝ፣ ራሳቸው የማያደርጉትን፣ ለምን ለሌላ ያስተምራሉ !" ሴትዮዋ ራሳቸውን ነቀነቁ።

"ጨዋታን ጨዋታ ያነሳዋል" አለ ካኖሬዎስ ጓደኞች አንዱ፣ "በዚያ ሰሞን ነው፣ አንድ የኔ የሥራ ጓደኛ እህት፣ ልትጠይቀው ከደሴ ትመጣለች። አስፈላጊዎቹ የመጓጓዣ ሠነዶች ሁሉ አላት። እንዳጋጣሚ፣ የሚኖርበት ቀበሌ ሹሞች አንዱ፣ ጉረቤት ነበርና፣ ይህችን እህቱን ሻንጣዋን ይዛ ከወንድሟ ቤት ስትገባ አይቷታል። ወይዘሮዋ እንግዝርት የመሰለች ደማም ናት። ቀኑን ሙሉ አድፍጦ ያመሸና፣ ማታው ገዳማ ላይ፣ ካንድ የሥራ ጓደኛው ጋር፣ ይህችን እንግዳ ለመጥለፍ፣ ወደ ጓደኛዬ ቤት ሲያመሩ፤ ጓደኛዬ ደግሞ በአዲሱ ደንብ መሠረት፣ ከቤት እንግዳ መምጣቱን ለማስገንዘብና ለማስመዝገብ፣ ወደ ቀበሌ ጣቢያ ለመሔድ ሲነሳ፣ ከበሩ ላይ እነዚህን የቀበሌ ሰዎች ያገኛቸዋል። እንግዲህ ተመልከቱ፣ ይቺ እህቱ

የወለደች፣ የከበደች፣ የሞቀ ትዳር ያላት፣ የቤት እመቤት ናት። ስለሁኔታው እዚያው እበሩ ላይ ለሁለቱም የቀበሌ ሹሞች ይነግርና፣ “እንዲውም ቀበሌው ጣቢያ ከመሔድ ዳንኩ፣ እናንተው መዝግቡና ፍቃዱን እዚሁ ስጡኝ !” ይላቸዋል። እነሱም፣ “እኛ ዛሬ ተረኞች አይደለንም ተረኞቹ እዚያው ቀበሌ ጣቢያ ይገኛሉና ሔደህ አስመዝግብ !” ይሉታል። እሱም መስሎት፣ ሊያስመዘግብ ሲሔድ፣ እነሱ ከቤቱ ገብተው፣ እንግዳዋን፣ “ያለፈቃድ ነው የመጣሽውና ለጥያቄ ትፈለጊያለሽ” ብለው በመውሰድ፣ ላልተወሰነ ጊዜ፣ ባልታወቀ ቦታ ሞሽረዋት ይባጃሉ።

“ያ መንድሟ፣ ያን ዕለት ማታ፣ ቀበሌ ካገኛቸው ሌሎች ሹማምንቶች ጋር ተነጋግሮ፣ አስፈላጊውን የእንግድነት ፈቃድ አግኝቶ፣ እቤቱ ሲመለስ ካጣት ጀምሮ፤ ሰማይ ቢቧጥጥ፣ ጮቤ ቢረግጥ፣ ለሣምንት ቀይታ ሊያገኛት አልቻለም። እየተፈራረቀ ስምንት ቀን ሙሉ፣ ውልቅልቋን ካወጡ በኋላ፣ ተጠርጥራ ምርመራ ላይ መቆየቷን በመግለጽ፣ ከሣምንት በኋላ አምጥተው ያስረክቡታል። እሱም ለጊዜው የሚያደርገው ተደናግሮት፣ እህቱን እንዳገኘ ለወጉ ያህል እንኳ ሳያስተናግዳት፣ ሳትውል ሳታድር፣ ባስቸኳይ ወደ ደሴ ይልካታል። በእህቱ ውርደት ቂም መያዙን የተረዱ፣ እነዚህ አለሌ የቀበሌ ሹሞች፣ በዚያ ጓደኛዬ ላይ የሆነ ያልሆነ ወንጀል ፈጥረው፣ ውህኒ ካስገቡት፣ ይኸው እዚያ ሆኖ ሲማቅቅ፣ አራተኛ ወሩን ይዟል።”

“አይደረግም አይባልም” አሉ ሴትዮዋ፣ አፋቸውን ከፍተው ሲያዳምጡ ቆይተው።

“እያዩዋቸው ! ይኸው እናንተ ለጥቂት ስዓቶች ለማፅናናት መጥታችሁ፣ እዚህ መገኘታችሁን አውቀው አይደል፤ እንዳያችሁት፣ “እናትህን መርሳት ይኖርብሃል”፣ ብለው ሲለፋደዱ ቆይተው የሔዱት ! እኔ እንደነሱ፣ ድንኳን አስተክዬ፣ ደርዘኖች መጠጦች አስደርድሬ፣ ደረት ምቱልኝ አላልኩ! ያለጠባዬ ጠባይ ፈጥረው፣ እንዳልቀብራት አረጉኝ።





“አዬ ልጄ፣ አኖሬምስ ! እነዚህን ርሳቸው ! ታግሰህ ትዳርህን መመሥረት ይሻላል” አሉ ----


“ጐረቤቴ ኢንጂነር ዘካርያስ የሰጠን ትምህርት፣ አማራጭ የማይገኝለት የዘመናችን ሐቀኛ ርምጃና ውሣኔ ነው። ሁኔታዎች እስኪያመቹልኝ ድረስ እዘገይ ይሆናል እንጅ፣ ቀራጡ ዘካርያስ የቀደደልን አውራ ጐዳና፣ ለኔም መጓዣ መሆን ያለበት፣ ጥርጊያ መንገዴ እንደሆነ ወስኛለሁ። መሠናክል በሌለበት ትክክለኛ ጐደና ላይ ለመጓዝ፣ የማይመርጥ ማን አለ።

-------❋▲❋▲❋✱❋ ------





# ብድር በምድር !



ኦፌ-ፋርሰን ቢነክስ፤ከደሊ ተንኮለኛ!
ሰዎች ተማፀነች፤ብታገኝ መጻኛ።
መጥኝታዋም ቢሆን፤ምላሹን አገኝቶ፤
ከከደሊ መንጋጋ፤አላቋታል ዋቶ።
ስዚያ ለፈፀመው፤የሰው ልጅ ውለታ፤
ከሩቅ ሀገር ሔዳ፤ተንገላታ አምጥታ፤
"ወይኔን እንኪ!"ብላ፤ ከፍላለች ወሮታ!
ያ ወይኒ ነው አሉ፤እስከ ዛሬ ድረስ፤
ሰውን እያረካ፤ በተለየ መንፈስ፤
አንዳንዶችን ሲያሥቅ፤ሌሎች የሚያስለቅስ!

# ም ራ ቂ

ይቺን ቍንጽል ድርሣን የተረጐምኋት፣ በቻይንኛ ከተፃፈ የምድረ-ፋርስ ትንግርታዊ መጽሐፈ-ታሪክ ውስጥ ነው። ለሃገሬ ኢትዮጵያ አንባብያን እንደሚጥም አድርጌ ማቅ ረቤን፣ አንባቢ ሁሉ እንደሚረዳልኝ አምናለሁ። በመሠረቱ " መተርጐም " ማለት *" A translation is not just a simple substituition of words. It involves the transfer of a massage from one culture to another in such a way that the readers can understand exactly what the writer intended to communicate. Two countries are not alike. Differences in landscape, climate. history, politics and tradition produce different cultures; the very same cultures which inturn shape people and society in this modern day. "* ስለሆነ፣ ትረጉም ሁለንተና ባሕርያቱን ማቀፍ ይኖርበታል። ይህችን መሰል ትርጉመ-ታሪኮች በብዛት ስላሉኝ፣ የአንባብያንን የፍላጐት መጠነ-ትርታ እየተከታተልኩ፣ በየጊዜው ላሳትማቸው ተዘጋጅቼአለሁ።

# ብድር በምድር !

ከምድረ ፋርስ ብርቅ
ታሪኮች አንዱ

የወይን ጠጅ
ቅድመ ታሪክ

ሐራት፤ በምድረ-ፋርስ የምትገኝ አንዷት ደማቅ መን ደር ነች። አያሌ ታሪኮችን አሳልፋ፤ ዛሬም አለች። ለህላዌዋ ምክንያት የሆናት አንድ የፋርስ ንጉሥ ነበር። ዝናውና ገና ናነቱ የጊዜውን የጐረቤት ሀገሮች ሁሉ ያሸብር ነበር። ይህ ኃይለኛ ንጉሥ ሻሚራን ይባላል። የጦር ሠራዊቱ ብዛት፤ ለቍጥር ያስቸግር ነበር። የመንግሥቱ ሀብትና ንብረት ይህ ነው አይባልም። ንጉሡን በዘመኑ ዝና ያተረፈለት፤ ኃያልነቱ ብቻ ሳይሆን፤ ብልጽግናው ጭምር ነው። ሠራዊቱም ሆነ ሕዝቡ ተንደላቆ ይኖር ነበር። በዚያ ጥንታዊ ዘመን ውስጥ መንግሥታዊ መዋቅሩ ተሳክቶለት፤ ሕዝባዊ አስተዳደሩ ተደላ ድሎለት የሚኖር ንጉሥ፤ እንደ ሻሚራን ያለ አልነበረም። ይበልጥ ደግሞ ተሟልቶለታል ያሰኘው፤ በችሎታውም ሆነ በጉልበቱ ይህ ቀረው የማይባል መሰል ልጅ የነበረው መሆኑ ነው። በአልጋ ወራሽነት የታጨው ይህ ልጅ፤ ተኵሶ የማይ ስት፤ ተናግሮ የማይሳሳት፤ ጠላት ይዞ የሚወቃ፤ ተቃራኒውን ሁሉ የሚደቃ፤ መሆኑን በየዕለት ድርጊቱ ያሥመሰከረ ነበር። ንጉሥ ሻሚራን ባድሐም ከሚባለው ተኵሶ ከማይስት ልጁ ጋር በተድላ ደስታ፤ በባዝግናና በእንቀኍ ተንቆጥቁጦ በተሠ ራው ቤተ-መንግሥት ባንድነት ይኖሩ ነበር።

ከዘመናት በአንደኛው ቀን፣ ንጉሥ ሻሚራን ከሚወደው የቤተ-መንግሥቱ ባልኮኒ ላይ ዙፋኑን አዘርግቶ ታላቅ ግብዣ ያደርጋል። በዚሁ ዕለት ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ሌላ፣ የቅርብ ባለሟሎች የሆኑት ሁሉ ከበረንዳው ሥር በተንጣለለው ፀአዳና ማራኪ መስክ ላይ፣ የዚህ ታላቅ ፈንጠዝያ ግብር ተካፋይ በመሆን ተገኝተዋል።

ያለወትሮው፣ በዚያን ቀን የተተከለ ድንኳን ወይም የተጣለ ዳስ አልነበረም። የቀኑ ፀሐይ ፈንጥቃ፣ ወደ ማለዳው ላይ ነበር። በቤተ-መንግሥቱ አድማሣዊ ዙርያ ገረገንብ ባለው ያታክልት መስክ ላይ የተሠተሩት ተክሎችና ጽጌያት፣ አዕይንትን ከመማረክ አልፈው፣ የያንዳንዱን ተጋባዥ አፍንጫዎች ሁሉ በመዓዛቸው አሥክረውታል። በቅይር ቅርፅ ከተኰለ ኰሉት የግብር መቀመጫዎችና ጠረጴዛዎች ሌላ፣ ሰፊው መስክ፣ ብዙ እንግዶችን በመድረክነት ጭምር ለማገልገል ይሆነኝ ብሎ የተሠራ ነው። ከመስኩ ምሥራቃዊ ጠርዝ ላይ፣ ገብታችሁ ተንቦራጨቁብኝ እያለች የምትጋብዝ መሳይ መጠነኛ ኩሬ፣ በአርምሞ ለጥ ብላ ትታያለች። ከበስተዳርቻዋ እየተንጠራዋዙ የሚዝለገለጉ ሐምራዊ ሐረጎች፣ ረባዳውን ቦታ እየፈለጉ ተሽሎክልከው በመኃዝ፣ በቤተ-መንሥቱ የጀርባ ሕንፃ ላይ ተሠይመዋል። ውበታቸውን ያየ፣ እህል ውሃ አያሰኘውም። ለኬክሮስ ቆይታ ያህል እያረፉ፣ ወደላይ እንደ ርችት የሚተኰሱ ምንጮች ከሐይቁ እንብርት ላይ፣ ሿ ተምቧ እያሉ፣ በሕብረ ቀለማት አሸብርቀው፣ ልዩ ትርዒት ከመስጠታቸውም በላይ፣ ከዕዝልና አራራይ በተቀመረ ፀዋትወ-ዜማ ስልት ልዩ ጣዕመ-ሙዚቃ ይለግሳሉ። በዚያች አነስተኛ ኩሬ ላይ እንደመኖርያ ገዳማቸው አርገው የሚንሳፈፉትን ልዩ ልዩ ዓሣዎችና አዕዋፋት መመል





ከት፣ ታይቶ የማይጠገቡት ትርዒት ነው። የዕለቱ ግብር ተከናውኖ፣ በዚያች ውብ መስክ ላይ የባሕሉ ሙዚቃና ጭፈራ ሊጀመር ሲል፣ ከዚህ ቀደም በዚያ ታላቅ ቤተ-መንግሥት የመስክ መድረክ ላይ፣ በዚያ ሁሉ መኳንንትና ሠራዊት ፊት፣ ንጉሡ ከነቤተሰቦቹ በዙፋኑ ላይ እንዳለ፣ ተደርጎም ሆነ ተሰምቶ የማያውቅ፣ አንድ አስደናቂ ድርጊት ተፈፀመ።

ከዚህ መጣች የማይሏት አንዲት በውበቷ የምታባባና የምታሳዝን ፎኒክስ ከወደሰማይ ተምዘግዝጋ ንጉሡ ከተቀመጠበት ባልኮኒ (በረንዳ) እጅታ ላይ ታርፋለች። ወርቅማ ላባዎቿ ከሰማያት የወረደች አስመስለዋታል። በደረቷና በአክናፎቿ ላይ የተነደፈው ሽልምልሞቿ ምድራዊ እንዳልሆነች ይመሰክራል። በበረንዳው ላይ ብዙ ሳትቆይ፣ ፈጥና ለባሕላዊ ዝግጅት ወደተሠናዳው የመስክ መድረክ ላይ ከማዕከሉ ታርፋለች። ይህችን ፎኒክስ አስቀድሞ ከዚያ ሁሉ ሠራዊት ያየ ንጉሡ ነበረ። ለህያውነትና ለዘለዓለማዊነት ምልክት በመሆን የታወቀችው ያቺ ፎኒክስ፣ በዚያ የቤተ-መንግሥት አደባባይ ላይ መገኘቷ አለብርቱ ምክንያት አልነበረም። የተራበ እባብ በመላ አካላቷ ላይ ተጠምጥሞ፣ ሊገድላትና ሊመገባት ይታገላት ኖሯል። ከይሲው ባስከተለው ትንቅንቅ ሳቢያ፣ የፎኒክሷ ላባዎች በመጠኑ መነቀልና መነጨት ደርሶባቸዋል። በዚያን ወቅት “ ክንፌ አውጭኝ! ” በማለት፣ ከንፋ ባደባባዩ መገኘቷ፣ “ ሙጥኝ፣ አድኑኝ፣ ” ለማለት ነበር። ያ ሁሉ ሠራዊት፣ ሳያስበውና ሳይጠብቀው፣ ያ አሳዛኝ ትርዒት ድንገት ሲያጋጥመው፣ የሚይዘውና የሚሠራው ጠፍቶት ተሸበረ። አስቀድሞ አይቶ የነበረው ያ ንጉሥ ግን፣ ለጠቅላላ ሠራዊቱ

እንዲረጋጋና በያለበት እንዲቀመጥ ትዕዛዝ ካስተላለፈ በኋላ፣ በተኳሽነት ለታወቀው ልጁ ፈጥኖ እንዲህ አለ።

" ልጄ ባድሀም! ዛሬ የሙያህ መፈተኛ ቀን ነው። የተቸገረ ሰው ሳይሆን፣ በሥቃይ የተያዘች ፎኒክስ የኛን ርዳታ ለማግኘት መጥታለች። ምናልባትም ይህን ርዳታ ለማግኘት ብዙ ርቀት ተጕዛ ይሆናል የመጣችው። በዚያ ሁሉ ጉዞዋ፣ የሚረዳት ሰው ሳይኖር ቀርቶ አይደለም። እንግዲህ እመረኝ። ከዚሁ ከበረንዳው እንዳለህ፣ የከይሲውን መርዘኛ ጭንቅላት አነጣጥርና ቀንጥሰህ ጣልልኝ!! እኛን መርጣ፣ ሙጥኝ ለማለት የመጣችዋን ይህችን የዋህ ፎኒክስ ከጭንቀቷ ገላግላት! እግረ መንገዱንም፣ ይህንን አጋጣሚ ተአምር ለማየት የታደለው ሠራዊታችንና መኳንንታችን፣ ግብሩን እየበላ ታሪኩን ይመዝግብ" አለና ከወርቅ የተሠራ የገዛ ራሱን ሽጉጥ ከትጥቁ ፈትቶ ሰጠው። ባድሀምም አፍታም አልቆየ፣ ያባቱን ሽጉጥ ተቀብሎ ከመቅጽበት አቀባብሎ ወደ ፎኒክሴዪቱ አቅጣጫ ደገነ!!

" አደራህ ልጄ! ምናልባት ስተህ፣ ከእባቡ ይልቅ ፎኒክሷን እንዳትገድልብኝ!" በማለት ንጉሡ እንደገና አስጠነቀቀው። የፎኒክሷ አሳዛኝነት ያባባው ሆዱ አላስችል ብሎት።

" አባባ በኔ ይሁንብህ! ይህ ላንተ ብቻ የቀረበ ፈተና ሳይሆን፣ ለታሪክም የተላከ መፈታተኛ ነው!" ሲል መለሰ። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ፎኒክሷ ከእባቡ ጋር ትታገላለች። እባቡ ጡንቻዎቹን ባኰማተረውና ባጦዘው ቍጥር፣ ፎኒክሷ አቅም እየተሳናት ከቆመችበት ለመውደቅ ትንገዳገዳለች። ይህም ሁኔታዋ፣ ለባድሀም ኢላማ ማነጣጠር መለስተኛ ችግር ሆኖበት ከቆየ በኋላ፣ በዚያው ወቅት እባቡ ራሱን ወደ ፎኒክሷ ጭንቅላት ለማምራት ሲንጠራራ፣ ቃታውን ሳበ። የባቡ ጭንቅ





ላት ተቀንጥሶ በመስኩ ላይ ሲወራጭ ከታየ በኋላ ነበር፣ የተኰሰው ጥይት ጩኸት እንኳ የተሰማው። ቀሪውን የእባብ ዐካል በኩንቢዋ ካላቀቀችና፣ በመስኩ ላይ ከጣለች በኋላ፣ ተጨብጦ የቆየውን ዐከሏን ለማንቀሳቀስ ያህል ክንፎቿን አራገበች፣ ለምስጋና ያረገችው ይመስላል፣ ሦስት ጊዜ ያህል ንጉሡ የነበረበትን ዙፋን ዞራ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ከነፈች። አራግፋው ከነበረው ላባዋ ለማግኘት፣ በቤተ- መንግሥቱ አደባባይ የነበረው ሠራዊት ሁሉ ተሻማ!! ንጉሡም፣ በሕዝቡ መሐል ለነፍጠኛ ልጁ ምሥጋና ካቀረበ በኋላ፣ የዕለቱ የሙዚቃ ድርጅት እንዲቀጥል አዘዘ። ያን አስደናቂ የፎኒክስ ትንግርት በአንክሮ ሲመለከት የቆየው ሠራዊት፣ የፎኒክሷ ሥቃይ ከፈጠረበት ጭንቀቱ እፎይ ብሎ፣ በቤተ-መንግሥቱ ዘማርያን የቀረበለትን የሙዚቃ ድግስ ይከሠክስ ጀመር። የጭንቀቱን ያህል፣ በሙዚቃው ርካታ ተዝናንቶ፣ ከዝግጅቱ ፍፃሜ በኋላ በደስታ ወደየቤቱ ተሠማራ።

እንስሳትና አእዋፋትም እንደባለኅሊናው ሰው የዘመን መሥፈርያና ካላንደር ያላቸው ይመስላል፣ ያቺ ውለታ የተደረገላት ፎኒክስ ወሮታዋን ለመክፈል ያቀደች ይመስላል፣ ርዳታ በተሰጣት ልክ በዓመቱ፣ በዚያው ሰዓትና ቦታ ከተፍ አለች። በዚያን ዕለት፣ ከወትሮዋ አምሮባት ወፍራና አሸብርቃ ነበር። ወርቅማና ሽልምልሙ ላባዋ በውበቱ ያየውን ዐይን ሁሉ ይገላምጥ ነበር። ዐይኖቿ የፀሓየ ብርሃን ፀዳል ያህል ያንፀባርቃሉ። ፀዳል ይረጫሉ። ንጉሡ በበረንዳው ዙፋን ላይ የተሠየመ ቢሆንም ብርሃን-ፀዳል ሲፈነጥቁ፣ የደስታ ብሥራት እንደነበር ያሳያሉ። የተጋበዘው መኳንንትና ሠራዊት ገና ውጭ ነበር። ያቺ ፎኒክስ፣ በንጉሡ ዙፋን አናት ላይ ሦስት ጊዜ ያህል በዝግታ ፍጥነት ከዞረች በኋላ፣ ያ

ጠላቷ እባብ ከተገደለበት ቦታ ላይ ሔዳ አረፈች። ቀን ቆጥራ በመምጣቷ፣ ንጉሡና ባለሟሎቹ ተጠንቅቀው የምታደርገውን ሁሉ በውል ይከታተሉ ጀመር። አስቀድማ በሁለት እግሮቿ ጥፍሮች መሬቱን ከኰደፈረች በኋላ፣ ከአንገቷ ቀና ጐንበስ በማለት ለንጉሡ እያመ ለከተች፣ ሦሥት ነጫጭ ፍሬዎችን ካፏ አውጥታ፣ ከቆፈረችው መሬት ላይ አስቀምጣ አፈር አለበሰችው። ይህን ካደረገች በኋላ፣ ንጉሡ ወደ ተቀመጠበት ዙፋን ተጠግታ የሚስረቀረቅ ድምፇን ካሰማች በኋላ፣ እንደለመደችው ሦሥት ጊዜ ዞራ፣ ወደመጣችበት ሄደች። ንጉሡም ወዲያው ፈጥኖ ሦስት ባለሟሎቹን፣ ያመጣችውን ሦስት ፍሬዎች ከቀበረችበት አምጥተው እንዲሰጡት ትዕዛዝ ሰጠ። ወዲያው ቀርቦለት ቢያይ፣ ከዚህ ቀደም አይቶ የማያውቀው የፍሬ ዐይነት መሆኑን ተረዳ። ለጊዜው ባካባቢው ካሉት ባለሟሎች ውስጥ፣ የየትኛው ተክለ-ዘር ወይም የየትኛው ዕፅ ፍሬ እንደሆነ ሊያውቅ የሚችል ሰው ባለመኖሩ፣ በሃገሩ የሚገኙትን የሥነ ዕፀዋት ሊቃውንት እንዲመጡለት ጥሪ አደረገ። ይህ በሆነ በሣልስቱ፣ የሀገሩ ሊቃውንት በጥሪው መሠረት ከቤተ መንግሥት መጡ።

ጉባዔ ሊቃውንቱ በተከፈተበት ወቅት፣ ንጉሡ የሚከተለውን መግለጫ አሰማ።

“ እነዚህ ጠንካራ ፍሬዎች በስጦታ የቀረበልን ከወዳጅ ወፍ ነው። ከዚህ በፊት ለፈፀምንላት ውለታ፣ ወሮታ እንዲሆንላት የሰጠችን መሆኑን እንገምታለን። ዝርዝር ታሪኩን ወደፊት ትረዱታላችሁ። አሁን ግን የምትረዱን ፍሬነቱ የምን ተክል እንደሆነ እንድትገልጡልን ነው። ምንስ ሆኖ እንዲጠቅመን ያበረከተችበትን ግልጋሎት ብትገልፁልን ደስታውን እንችልም ” በማለት ሦስቱን ፍሬዎች አቀረበላቸው።

ሊቃውንቱ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት፣ የፍሬውን ምንነት ለማወቅ ብዙ የምርመራ ሙከራዎች አደረጉ። ምንነቱን ግን በማየት ብቻ መረዳት እንደማይችሉ አረጋገጡ። በመጨረሻም ላይ፣ የተሰበሰቡት ሊቃውንተ-ቦታኒ በሙሉ (ሊቃነ-ዕፀዋት)፣ ፍሬዎቹ ተተክለው፣ በብርቱ እንክብካቤና ጥበቃ ካደጉ በኋላ፣ ቅጠላቸውን በማየት ምንነቱን መወሰን እንደሚቻል ለንጉሡ ተናግረው ተበተኑ። ንጉሡም በሉቃውንቱ ሐሳብ ተስማምቶ፣ በቤተ-መንግሥቱ ለታወቁ አትክልተኞች በአደራ ጭምር ተክለው እንዲያበቅሉ ፍሬዎቹን ሰጣቸው። ፍሬዎቹን በሰጠበት ወቅት፣ የሚከተለውን አደራ ጭምር ነግሮአቸው ነበር።

“ በዚሁ በግቢው ውስጥ በአንደኛው ያትክልት ቦታ ጥጋት ላይ ትክሏቸው። እንስሳም ሆነ ሰው እንዳያጠፋቸው፣ የተተከሉበትን ቦታ በጥንቃቄ እጠሩት። ባካባቢውም ወፎች እንዳይጠጉ በጥንቃቄ ተከላከሉ። ስለ እድገታቸውም በየጊዜው አስፈላጊውን ዘገባ አቅርቡልኝ። በትልቅ ተስፋ የምንጠብቀው፣ የፎኔክስ ልዩ ስጦታ ነው። አደራ! ”

የቤተ መንግሥቱ አትክልተኞች በተጣለባቸው አደራ መሠረት፣ ጠዋት ማታ ፍሬያቱን ሳይለዩ፣ በማጠጣትና በመኰትኰት ፍግ በመስጠት፣ በሚገባ ተከባከቡ። ብዙም አልቆየ፣ የተተከሉት ፍሬዎች እንቡጥ አፅቅ አቆጥቊጠው ብቅ አሉ። ይህ እንደሆነም፣ ተክለኞቹ ተፋጥነው ለንጉሡ አበሠሩት። ንጉሡም እንደሰማ፣ ሊቃውንቱን ባስቸኳይ ጠርቶ እንዲመረ

ምሩ አደረገ። ሊቃውንቱም ተሰብስበው ቆጽሉን ካዩ በኋላ፣ “እንዲህ ያለ ተክልም ሆነ ቅጠል ከዚህ ቀደም አይተንም ሆነ አጋጥሞን አናውቅም ” በማለት፣ ወደየቤታቸው ተመለሱ።

ከፍተኛ እንክብካቤ እየተደረገላቸው እድገታቸውን የወጠኑት እነዚያ ሦስት ፍሬዎች፣ ፈጣን የሆነ ለውጥ ማሳየት ጀመሩ። አደራ የተጣለባቸውም አትክልተኞች፤ ከመቸውም ይልቅ ንጉሡን ለማስደሰት ሲሉ፣ ተክሎቹ የሚያስፈልጋቸውን ውሃ፣ ሙቀት ግፍና ሌላም አልሚ ምግበ ተክሎች እጥፍ እያደረጉ እንክብካበያቸውን ቀጠሉ። የሚለገሣቸውን ስጦታ ሁሉ በከንቱ ያላስቀሩት እነዚያ ስሉሥ ፍሬዎች፣ ባል ተጠበቁበት ሰዓት፤ ቆፅላቸውን አቆጥቁጠው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። የበቀሉት ቀንበጦች መጠናቸው የበዛ፣ ተክላዊ ዐይናቸው ያጐረጠ፣ ዳጉሣ መሳዩ ለጋ ቅርንጫፋቸው ያንፈራጠጠ ሆኖ ተገኘ። ይህን የተስፋ ምጣት የተመለከቱ ተክለኞች፣ ሁኔታው አላስችል ብሏቸው፣ ስለ ፍሬዎቹ ማቆጥቆጥ ለማብሠር ወደ ንጉሡ ሔዱ። ንጉሡም ዘንድ እንደቀረቡ፤

“ በቤተ መንግሥቱ ጊቢ ውስጥ የማይገኙ የዕፀዋት ዐይነቶች አልነበሩም። በምድር ላይ የበቀሉ የዕፀዋት ዐይነቶች ሁሉ ከዚህ ቀደም አላመለጡንም። የተለያዩ ውብ ተክሎች በማስተናገዳችን ኩራት ይሰማን ነበር። ይሁን እንጅ፣ በትዕዛዝዎ መሠረት የተተከሉት እነዚያ ሦስት ፍሬዎች፣ ሌላ ውበትና ተፈጥሮ ያላቸው ሆነው ማቆጥቆጥ ጀምረዋል። ገና በእንቡጥነታቸው፣ ለጊቢውና ለሌሎቹ አትክልቶችም ግርማ ሞገስ በመሆን ልዩ ድምቀት እየፈነጠቁ ነው። እንኰራባቸው የነበሩትን የፋርስ ጽጌያት ሳይቀር እያስናቋቸው ነው። ለውበ





ታቸውም ሆነ ለዕድገት ፍጥነታቸው ምንም ዐይነት እንከን አይወጣላቸውም። ”

ንጉሡም ወዲያው እነዚያን ጠበብተ-ዕፀዋት አስጠርቶ ይዟቸው፣ ዕፀዋቱ ወደ ሚገኙበት ወሰዳቸው። ንጉሡም ሆነ ሊቃውንቱ ታዳጊዎቹን ዕፀዋት እንዳዩ ካድናቆት በስተቀር፣ በሕይወታቸው ዐይተውት የማያውቁት ተክል እንደሆነ ተናገሩ። ንጉሡም “ ምናልባት ያቺ ባለውለታ ፎኒክስ፣ ከምድር ዳርቻ ያመጣችው ልዩ ስጦታዋ ይሆናል። ሁላችንም በትዕግሥት መጠበቅ ይኖርብናል። ተክሎቹ ለዓቅመ-ፍሬ ደርሰው፣ ውጤቱን ካየን በኋላ ነው፣ የተክሉን ምንነት መለየት የምንችለው ” በማለት ተናገረና ሊቃውንቱን አሰናበተ።

የተወለደ ማደጉ፣ የተዘራ መብቀሉ፣ የተተከለ መፅደቁ የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ ነውና፣ እነዚያ ሥሉስ የፎኒክስ ስጦታ ፍሬዎች በቀሉ፣ አደጉ። አንጓቸው ሳይቀር አውቀው እንደ መዘዙት ያህል እያደር ተመነደገ። ቆፅሎቹ በየቀንበጣቸው ላይ አበቡ። ገና አበባቸው ታይቶ ሳይጠገብ፣ እምቡጥነታቸውን አልፈው ፍሬያቸውን አሳዩ። እያደር ጐመሩ እንጅ፣ ጅማሬያቸው ላይ ሐምራዊነት የሚፈነጥቅ ቀለም ነበራቸው። ውስጠ ውሃቸው፣ ይሆነኝ ብለው የቀመሙትና የጠመቁት ይመስል፣ አተኩሮ ላያቸው ሲላወሱና እርስ-በርስ ሲዋሀዱ በግልፅ ይታይ ነበር። ቀስ በቀስም ውህደታቸው ሠምሮ፣ ወፍራምና የረጋ ደም መሰል ፈሳሽ ይታይባቸው ጀመር። የእሸትነት አፍላ ዕድሜያቸውን እንዳገባደዱም፣ መጐምራታቸውን ለማሳየት፣ ፍፁም ጥቁር እርጎ መሰሉ። የተመለከታቸውን ሁሉ ቢያስጐመዥም፣ ቀጥፎ ሊበላቸው የደ

ፈረ አንድም ሰው አልነበረም። አንዱ ፍራቻ ምንነታቸው ያልታወቁ መሆናቸው ነበር። በመዓዛቸው ግን ሰዎቹ ብቻ ሳይሆኑ፣ መላው የቤተ መንግሥቱ ጊቢ ረክቷል።

ፍሬዎቹ በሙሉ ዕድገት በጐመሩበት ጊዜ፣ ወርኃ ዓመቱ በልግ ነበር። በዚያ በቤተ መንሥስቱ ቅጥር ጊቢ የሚገኙ ተክለ-ፍሬዎች ሁሉ የዐመቱን በረከት ያሚያበረክቱበት ወቅት በመሆኑ፣ ሁሉም አኰርተዋል። በተረሎሚው፣ ፖፖዬው፣ ብርቱኳኑ፣ ትርንጐው ወዘተ... ግሸጣውም በየበኩላቸው አፍርተው ከምግብነታቸው ሌላ ለሚመለከታቸውን አዕይንት ርካታ ይሰጡ ነበር። ጊቢውን የሚያውደው መዓዛቸው፣ ሌላ ሕይወት ይሰጣል። ይህ መዓዛና ትርዒት የማረካቸው አእዋፋት ሁሉ፣ በቤተ መንግሥቱ አናት ላይ ሲያንዣብቡ፣ ይውላሉ። የሚያስጠጋቸው ግን አልነበረም።

በከፍተኛ ጉጉት ሲጠባበቅ የከረመው ንጉሥ፣ ፍሬዎቹ ለመከር መድረሳቸው እንደተነገረው፣ በአንደኛው ቀን ከነአጀቡ ወደ ተክሎቹ ሔደ። ዘለላዎቹ ፍሬዎች ከመጐምራታቸው ብዛት የተነሳ ሙክክ ብለው በመብሰላቸው፣ አንዳንዶቹ አርግዘው የያዙት ፈሳሽ እየወጠራቸው ጧ ብለው ይፈነዱ ነበር። አሁንም ፍሳሻቸውን በማየት ይጐምጁ እንጂ ደፍሮ የቀመሳቸው አልነበረም። ንጉሡን አጅበው የተገኙት ሊቃውንትም፣ ያ ፍሬ የተክሉ ፍሬ መሆኑና በመጨረሻ የብስለት ደረጃው ላይም እንዳለ አረጋገጡ። ከመሓላቸው ምንነቱን ያወቀ ባይኖርም፣ ቀምሶ ለመረዳት የሞከረም ሆነ የደፈረ አልነበረም። ንጉሡ ግን በበኩሉ ያዘጋጀው እቅድ ስለ ነበረው፣ የደረሰ የደረሰውን ዘለላ፣ በዋድያት አጠራቅመው፣





እስኪኰመጥጥለት ድረስ በጥንቃቄ እንዲያስቀምጡ ላትክልተኞችና ለቤተ መንግሥቱ መጋቢ አለቃ ትዕዛዝ ሰጠ። ይህን ልዩ ትዕዛዝ ባስተላለፈ በሁለተኛው ወር ላይ፣ በዋድያት ከተቀመጠው ውስጥ የመፍላት ድምፅ በመሰማቱ፣ ለንጉሡ ተነገረው። ንጉሡም ወዲያው፣ ሞት ተፈርዶባቸው፣ ዕለተሞታቸውን ከሚጠብቁ ወንጀለኞች ውስጥ አንዱን ከእስር ቤት አስመጥቶ፣ ራሱ ንጉሡ ባለበት እንዲጠጣ ተደረገ። ያ ፍሬ መርዝነት ቢኖረውና ጠጭውን ቢገለውም፣ የሞት ፍርደኛ መመረጡ፣ በዚያው አድዮስ ቢልም ዋጋው እንጅ በደል እንደማይሆን ታስቦ የተደረገ ዘዴ ነበር። ያ እሥረኛ ግን፣ የመጀመሪያ ዋንጫውን እንደጠጣ፣ ኰሶ የጠጣ ያህል ፊቱን አኰማተረ። ጐምዛዛው የፍሬ ወሃ ጐመዘዘው፣ መረረው። ጕረሮውን፣ ላንቃውን፣ ትናጋውን፣ ከንፈሩንና ምላሱን ጭምር አንጣጣው። በዚህ ምሬት ያልተበገረው ያ ሸካራ ጥርሱ ብቻ ነበር። የጕረሮውን ቁልቁለት ወርዶ ከሆድ ባሕሩ ሲገባ ግን፣ ሌላ ስሜት ነበር የሰጠው። ወንጀለኛው በመጠጡ ጣዕም የተሰማው ስሜት በገፅታው ላይ ልዩ ሁኔታ ይነበ ብበት እንጅ፣ ሆዱን አልቈረጠውም፣ ወይም አልፈለጠውም። ይህን ሁኔታ በአንክሮ ይመለከት የነበረው ንጉሥ፣ ሁለተኛ ዋንጫ ይፈልግ እንደሆን እሥረኛውን ጠየቀው። ቆራጡ እሥረኛ ግን፣ መፈተኛ መሆኑን ባይረዳም፣-

"ታድዬ! አግኝቼ ነው እንዴ!" ሲል መለሰ። ንጉሡም ድገሙት አለና፣ ሌላ አንድ ዋንጫ ሙሉ ተሰጠው። አፍታም ሳይቆይ ዋንጫውን አፈፍ አርጐ እንደተቀበለ፣ ወዲያው ባንድ ትንፋሽ ጭውውው አርጐ ጨለጠው።

ከሆዱ መጠጡ እንደደረሰ፣ ድል ያለው ግሣት አሰማና “ እሠይ! ” አለ። ወዲይው ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ በመንሳት፣ ንጉሡን የዝንብ ያህል ሳይቆጥር፣ ይዘፍን፣ ይዘምር፣ ያቅራራ ይጨፍር ገባ። በሕይወቱ አጋጥሞት የማያውቅ ደስታ ጠቅላላ ሰውነቱን ወረረው። በፍፁም ደስታ ሰጠመ። ከተሠረገበት ዕለት ይልቅ ያ ወቅት አስፈነደቀው። ዘለለ ፈንጠዘ። አውታረ ሰውነቱ በተድላ ሲነዝሩ ተሰማው። ሕዋሶቹ ማሲንቆአቸውን ሲከረክሩ፣ ክራራቸውን ሲያከሩ፣ ከበሮአቸውን ሲደልቁ ተሰማው። ሕዋሳቱ በመላእክት እንዚራ ታጅበው በሕዋ ላይ ሲንሳፈፉና ሲከንፉ ታየው። እነኣርያም እነራማ ተበርግገው ወለል ብለው በራዕዩ ሳይሆን በውኑ ተከሠቱለት። የሚያየው ሁሉ ብርሃን የተጎናፀፈ፣ ፀጋ የለበሰ መሰለው። ባጠቃላይ ሰው ከመሆኑ ክልል የወጣ ልዩና ሌላ ፍጡር የሆነ ያህል መሰለው። የሚናገረው ጣመለት፣ የዘመረው ተሰማለት፣ ያደረገው ሁሉ ተደነቀለት። ያልነበረው ጉልበት ተሰማው። የመጀመሪያው ዋንጫ ቅምሻ ፊቱን በምሬቱ ያኰማተረበትን ያህል፣ ሁለተኛው ዋንጫ፣ ገፁን ብቻ ሳይሆን መላ ዐካሉን አቀላለት። ያጋሙት ፍም መሰለ። ገዳይነቱን ቀርቶ ወንጀለኛነቱንአስረሳው። እሰይ! እልል አለ....

ያን አስደናቂ ሁኔታ ያየ ንጉሥ፣ አላስችል ብሎት፣ እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ አንድ ዋንጫ እንዲጨመርለት ለማዘዝ ሲዘጋጅ፣ ከንጉሡ ቀድሞ እሥረኛው እንዲጨመርለት ንጉሡን እንዲህ በማለት ተማጠነ። “ በወለደችህ እናት! ሌላ አላስቸግርህም። ሌላ አንድ ዋንጫ እንዲሰጠኝ እለምናለሁ። የመጨረሻዬ ይሆናል። ከዚያ በኋላ የፈለጋችሁን ለማድረግ






ትችላላችሁ፡--- ብታርዱኝም ብትሠቅሉኝም እንደ ፈለጋችሁ! በሰው ልጅነቴ፣ መሞቴን በመወለዴ አውቀዋለሁ! መዋቲነቴን ልደቴ አስቀድሞ አስተምሮኛል-- ብቻ አንዲት የመጨረሻዋን ፅዋ አትንፈጉኝ! ”

ለመፈተኛ የተዘጋጀ መሆኑን ንጉሡ ያውቃልና፣ እሥረኛው የሚሆነውን ሁኔታ ሳይሆን፣ መጠጡ የሚያደርገውን ውጤት ለማየት ሲል፣ በእሥረኛው ጥያቄ መሠረት ሦስተኛው ፅዋ ተፈቀደለት። የመጨረሻውን ሦስተኛ ዋንጫ እንደጠጣ፣ ሆዱን ሳይሆን ራሱን ከበደው። ብዙም አልቆየም ወደቀ። ከወደቀበት ወዲያው እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ። ከዚያ እንቅልፉ የነቃው በሁለተኛው ቀን ማለዳ ላይ ነበር። ጠባቂዎቹ ባለሟሎች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት፣ እንደ ነቃ፣ ሲጠብቀው ወደ ነበረው ንጉሥ ዘንድ ወስደው አቀረቡት።

“ ትናንትና ምን ጠጥተህ ነበር ? ምንስ ዐይነት ስሜት ተሰማህ ? ” ስለነዚያ የፎኔክስ ፍሬዎች ውጤት ለማወቅ፣ በጉጉት የቆየው ንጉሥ፣ ለዚያ እሥረኛ ያቀረበለት፣ የመጀመሪያ ጥያቄ ነበር።

“ ምን ዐይነት መጠጥ እንደጠጣሁ አላውቅም። ግን በሕይወቴ ያላጋጠመኝ ከፍተኛ ጥሩ ስሜት ነበር የሰጠኝ። አርኪ ነበር!” በማለት ባጭሩ መለሰ። የመጠጡ ስሜት ገና አልለቀቀውም ነበር። ያለወትሮው ባንድ ቀን ውስጥ ሴሉ-ደሞቹ አብበውና ለምልመው ማደራቸው፣ በዚያ ወቅትም ይሰማው ነበር። ሰውነቱ ሳይቀር ልዩ መዓዛ ይረጭ ነበር።




ላለም ወይን መገኘት፣ መነሻው ምክንያት፣
ያ ከዶሲ ከሆነ፣ከሳችው መሠረት፣
ይወጣው ይሆናል፣ጠቃሚ መድኃኒት፤
በዘዴ ጨብጦ፣በጥበብ ቢጨምቁት!






“ ንጉሥ ሆይ፤ ፈቃድዎ ቢሆንልኝ፤ ዛሬም ቢለገሡኝ ምኞቴ ነው! የመጀመሪያዋን ፅዋ ስቀምስ፣ የአሲድ ጣዕም ያህል ምሬቱ ጐምዝዞኝ ነበር። ባሕረ ሆዴ በደረሰ ጊዜ ግን እንድደግም አሰኘኝ። ሁለተኛው ጽዋ ሲደገመኝ፣ ተዝናና ዝፈን ጨፍር የሚል ስሜት አሳደረብኝ። አብሮኝ የኖረው አፋርታምነቴ፣ ዐይነ ጥላዬ ለቆኝ ሲሄድ ታየኝ። ያን ጊዜ ነበር፤ ይህ ዐለም ለሰው ልጆች መደሰቻና መፈንጠዥያ ልዩ ሠገነት ሆኖ ያገኘሁት። ይህን ዕድል ሳላገኝና ጠበሉንም ሳልቀምስ ብሞት ኖሮ ምንኛ በቆጨኝ ነበር!! ” በማለት አድና ቆቱን ካንጀቱ ገለጠ።


ንጉሥ ሻሚራንም፤ በዚያ እሥረኛ ኖሙናንት፤ የዚያችን ባለውለታ ፎኤክስ ወ ሮታዊ ስጦታ ምንነት መረዳት ብቻ ሳይሆን፤ “ መጠጥ ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመጀ መሪያ ጊዜ ተማረ። ይህ በተገለፀለት በሣምንቱ፤ ከዚያ በፊት ተደርጎ ያማያውቅ ከፍተኛ የፌስታ ድግስ አርጎ፤ መሳፍን ቱንና መኳንንቱን በዚያ የወይን ጠጅ አሰከረው። እሱማ የሚነቃበት ጊዜ እስኪጠፋበት ድረስ በየቀኑ ይጐነጭ ጀመር። “ ወይን ያስተፌስህ ልበ ሰብ ” የሚለውን የመኢጠማ እውቅ መፈክር (መርሖ) በመቀየር “ ወይን ያስተፌስህ ሴለ-ሰብ ” ያለው ይኸው ንጉሥ ሳይሆን አልቀረም። ታዲያንን፤ ከዚያ ሁሉ የፌስታ ግርግርታና፤ ያጋጣሚ ትንግርት ውስጥ በጣም የሚገርመው፤ በዚያ ታላቅ የወይን ጠጅ በዓል ላይ፤ አስገኝዋ ፎኤክስ፤ ሽልማቱና ሌላው እንኳ ቢቀርባትም ቅሉ፤ በእንግ ድነት ወይም በተጋባዥነት አለመገኘቷ ነበር!!



ቤተ-መንግሥት ይኋል ፣ እንደዚህ ነው እንጅ
ወይንን ያስመረተ ፣ ለ" ሴል " የሚበጅ!




እንዳቅሙ ጠጥቶ፤እንዲረካ ባለም!
እኔ ብለግሠው ፤ ወይን ያለው ልዩ ጣዕም!
ሰክሮ ይረብሻል፤አንዳንዱ ድንባዣም!



# ክንፍማ ቢኖረኝ

ክንፍ የለሽ ሆኜ እንጅ ፤ ክንፍማ ቢኖረኝ
መቼ ያስችለኝ ነበር ፤ እኔ እንቺን ሳልጎበኝ??
    መቼ ያስችለኝ ነበር ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ፤
    ያችን ውብ ሀገሬን ፤ ሳላይና ሳልደርስ!
ከምድር ጥጋት ሆኖ ፤ ያሰሁበት ጋጣ ፤
ርቀት ድል መታኝ ፤ ስታገል ልመጣ!
    ተቸግሬ እንጅ ነው ፤ ሉንጎው እግሬ ቢያጥር ፤
    አለያማ በርግጥ ፤ እጎበኝሽ ነበር ።
እንደ ወፎቹማ ፤ ኖርኝ ቢሆን ያ ክንፍ!
ባልዘገየሁ ነበር ፤ እዚህ ስንከራፈፍ!
    በርሬ አያት ነበር ፤ ምን ዜቅ እንደዋጣት
    ጉስቁሏን ሀገሬን ፤ እርግብግቧን እናት!
ተባራሪ ወሬ ፤ ከሚያላግጥብኝ ፤
ከንፌ አያት ነበር ፤ ክንፍማ ቢኖረኝ!!
    ኧረ አዕዋፋት ፤ ክንፋችሁን ልዋስ ፤
    ሀገሬን አይቼ ፤ ደርሼ እስክመለስ ።
ንጿንማ ሆኜ ፤ ብገባ ከሀገር!
የናቱን ተባዮች ፤ በጠዘጠዝኩ ነበር!